በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና

ስታትስቲክስ ሥርዓት ጥቅምና አስፈላጊነት፣

አደረጃጀትና የመረጃ ፍሰት ሥርዓት

# የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ

*(ረቂቅ)*

የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
አዲስ አበባ፣ ጥር 1995

# በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ጥቅምና አስፈላጊነት፣ አደረጃጀትና የወረዳ ፍሰት ሥርዓት

(ረቂቅ)

# የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ

የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
አዲስ አበባ፣ ጥር 1995

## የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለግለሰቦች፣ ለቤተሰቦችና ለመንግሥት ምን ዓይነት የህግ፣ የአስተዳደርና የማህበራዊ አገልግሎት ጥቅሞችን ያስገኛል?

- ✓ እያንዳንዱ ዜጋ በህጋዊ ሰው ተለይቶ በመንግሥት ሰነድ የመታወቅ መብቱን ለማረጋገጥ፣ ማንነቱን በሚመለከት ለሚነሱ የህግና የአስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ የህፃናት ወላጆች ማንነት በመንግሥት ሰነድ እንዲታወቅ በማድረግ ልጆች ከወላጆቻቸውና ከማህበረሰቡ የሚፈልጉትን ገለጋሉት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል፤
- ✓ ማንኛውም ሰው በሀገሪ ህግ መሠረት ዜግነቱ በመንግሥት አስተዳደር የዜጎች ሰነድ ውስጥ በማያጠራጥር ሁኔታ እንዲመዘገብ ያስችላል፤
- ✓ ልጆችን ከልጅነት ጋብቻ ለመከላከልና ያለዕድሜአቸው ጋብቻ እንዲፈጽሙ ከተገደዱ በህግ ፊት መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል ቋሚና ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ወጣት አጥፊዎች በትክክለኛ ዕድሜአቸው ላይ የተመሠረተ ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግና እውቅና የተሰጣቸውን ሰብዓዊ መብቶች ለማስጠበቅ የሚያስችል ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ ወይም ጋብቻው ሲፈርስ የሚከሰቱ የመብት መጣሶችን ለመከላከልና ተገቢውን የአስተዳደርና የህግ ውሳኔ በአፋጣኝ ለማስጠት የሚያስችል ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በእድሜአቸው እንዲጀምሩና መንግሥትም እያንዳንዱ ህፃን ይኸ መብቱ መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ህፃናት ከተወለዱ ጀምሮ ከእናታቸው፣ ከቤተሰቡና ከመንግሥት ሲያገኙ የሚገባቸውን የጤና እንክብካቤ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቋሚ የመረጃ ሥርዓት ያስገኛል፤
- ✓ መንግሥት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የሞት መጠን የመቀነስ ሀላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል የሚረዱ የሞት ምክንያት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ አንድ ግለሰብ በመሞቱ ምክንያት ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ የሚደረጉ የንብረት ውርስ ጥያቄዎችን በህግ ፊት አፋጣኝ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ህጋዊ መረጃዎችን ያስገኛል፤
- ✓ የአንድ ሀገር ዜጎች ወደ ውጭ ሀገር ለመጓዝ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የጉዞ ሰነዶች ለማዘጋጀት የሚያስችል ህጋዊ የማንነት መረጃ በመንግስት ሰነድ ለማስቀመጥ ያስችላል፤
- ✓ የመምረጥና የመመረጥ መብትን ለመጠቀም የእያንዳንዱ ግለሰብ የዕድሜ፣ የዜግነትና ተመሳሳይ የማንነት መረጃዎች በመንግሥት ሰነድ ተመዝግበው እንዲገኙ ለማድረግ ያስችላል፤
- ✓ እስከ ቀበሌ መስተዳድር የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን ለማጠናቀር የሚያስችል ቀጣይና ወቅታዊ መረጃ ያስገኛል፤

## ማውጫ


**I** በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነት ምዝገባዎች ጥቅምና አስፈላጊነት ........................ 1

**II** በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ምን ዓይነት ይሆን?............................ 35

**III** በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል ምን ዝግጅት ተደርጓል? ........................... 42

**IV** በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ግለሰባዊ መረጃዎችና የስታትቲስክስ መረጃ ፍሰት አደረጃጀት ምን ዓይነት ይሆን? ...................................... 50

**V** የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በማቋቋም የምዝገባ ተቋማት እና ዋነኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋና ዋና የተግባር ዘርፎች ........................................ 55

# I በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነት ምዝገባዎች ጥቅምና አስፈላጊነት

## መግቢያ

በሰዎች ማህበራዊ አኗኗር ታሪክ ውስጥ ከሶስት ምዕተ አመት በላይ ያስቆጠረው የኩነቶች[1] ምዝገባ ሥርዓት፣ ሰዎች ማህበረሰባዊ አስተዳደራቸውን ወደ ተሻለ የአፈፃፀም ደረጃ ለማድረስ የሚያስችላቸውን የህዝብ አስተዳደር መሠረት ለመጣል ያደረጉት ረጅም ማህበራዊ ትግል አካል ነው። ይኸውም የማህበረሰቡ አባላት በግልና በጋራ በዋንኛነት በእኩልነት፣ ፍትሀዊና ጥሬት ቆጣቢ በሆነ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲተዳደሩ የሚያስችል አሰራር ከመፍጠርና ከማሳደግ ፍላጎት ጋር የተቆራኘ ነበር።

የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ምዝገባ አስፈላጊነት መሠረታዊ መነሻ ግለሰቦች በዜግነታቸው በአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን መብት ለማስጠበቅ ሆኖ በተለያየ ጊዜያት በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደነገጉትን የሰብዓዊ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎችን ለግለሰቦችና ለመንግሥት ለማስገኘት ጭምር ነው። የህዝብ አስተዳደር አመራር ስልትና ዕውቀት አንድ መንግሥት የሚመራውን ህዝብ በግለሰብነትና በማህበረሰብ አባልነት በመረጃ ለይቶ ከማወቅ ይመነጫል። ግለሰባዊ የህግና የአስተዳደር መረጃ አግባባዊው የመረጃ ምንጭ ደግሞ የወሳኝ ኩነቶች[2] ምዝገባ ስርዓት ነው። በመሆኑም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሌላቸው መንግሥታት የማስተዳደር ዕውቀት ምንጭ ስለሆነው ህዝብ የዕለት ተዕለት አኗኗር የሚገልጽ ወይም የሚያስረዳ የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት ሊኖራቸው አይችልም።

---

[1] ኩነት ማለት መከሰት፣ መፈጠር፣ . . .

[2] በዚህ ጽሁፍ ወሳኝ ኩነቶች የተባሉት ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው። እንደ ተባበሩት መንግስታት ትርጓሜ የሽል ሞት፣ ጉዲፈቻ፣ የጋብቻ መከናወን መሰረዝ፣ . . . ያጠቃልላል።

በአንድ ሀገር አግባባዊና ዘመናዊ የሕዝብ አስተዳደር ስርዓትን ለማስፈን ዜጎችን ከመንግሥት ጋር በሁለት ዘርፎች ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ይኸውም ዜጋው እንደግለሰብነቱ በቀጥታና እንደ ማህበረሰብ አባልነቱ በመንግሥት ተቋማት አማካኝነት ከመንግስት ጋር ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችለውን ህጋዊ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት ማደራጀትን ይጠይቃል። ይህን አሠራር በአንድ ሀገር ለመዘርጋት ሁለት የመረጃ ግብዓቶች በመሠረትነት ያስፈልጋሉ። እነርሱም ቀጣይና ቋሚ "ግለሰባዊና ህጋዊ የኩነቶች መረጃ" እና "ጥቅል የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች" ናቸው። ይህ አግባባዊ እና ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር አመራር ዕውን ሊሆን የሚችለው የህዝብ አስተዳደር አፈፃፀም ምሪቱ መሠረት የሆኑት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች በጽሁፍ በተደገፉ ግለሰባዊ የኩነት ህጋዊ መረጃዎች ላይ ሲመሠረቱና ከነዚህ ግላዊ መረጃዎች በመነሳት በተቀነባበሩ የስታቲስቲክስ መረጃዎች ማህበረሰቡን ወደ መምራት ደረጃ ላይ ሲደርስ ብቻ ነው። ይህም የሕዝብ አስተዳደር አሠራር መንግሥት የዜጎችን ግላዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን በህጋዊና አግባባዊ አስተዳደር ለመምራት የሚያስችለው ከመሆኑም ባሻገር የሚያስተዳድራቸውን አካላት ምንነትና ማንነት ለመለየትና ግለሰቦች ከማህበረሰባዊ ውክልናቸው አልፎ እንደግለሰብነት በሕዝብ አስተዳደር ምሪት ውስጥ የሚካተቱበትን የአሠራር ስልት በሥርዓትና ወጥነት ባለው መልኩ ለመንደፍ ያስችለዋል። በአንድ ሀገር ውስጥ የእነዚህ መረጃዎች በአንድነት መፈጠር የሀገሩ የሕዝብ አስተዳደር ተቋም በዋነኝነት ዜጎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው መከበራቸውን ለመከታተል እንዲችሉ ከማስቻላቸውም በላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮቻቸውና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎቶቻቸው በወቅትና በብቃት መተግበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓትን ለማስፈን ያስችላሉ።

እንደሚታወቀው የሕዝብ ቆጠራና የሥነ-ሕዝብ የናሙና ጥናቶች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ ሕዝባዊ ዕቅድ አውጪዎች መሠረታዊ የመረጃዎች ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ።/የሕዝብ ቆጠራ በአመዛኙ የዓለም ክፍል በየ10 ዓመቱ የሚካሄድ ሆኖ የአንድን አገር ወይም የተወሰነን ክልል አንድን ወቅት የተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን የናሙና ጥናት ደግሞ በናሙና የተመረጡ ቦታዎችን የተመለከተ መረጃ የማግኛ ዘዴ ነው። በመሆኑም ሁለቱም የመረጃ ምንጮች የየዓመቱን

የሕዝብ ብዛትና የዕድገት መጠን መረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ አያስገኙም። ከዚህም በላይ በቆጠራዎችና በናሙና ጥናቶች የሚሰበሰቡ የኩነት መረጃዎች ወዲያው ኩነቶቹ እንደተከሰቱ ሳይሆን ከተከሰቱ ከረጅም ጊዜ በኋላ በመሆኑ እንደሚፈለገው ወቅታዊና ጥራታቸው አስተማማኝ የሆነ መረጃ አያስገኙም።

ከላይ እንደተገለፀው በሕዝብ ቆጠራና በናሙና ጥናት አማካይነት በየዓመቱ ስንት ልጅ እንደተወለደ፣ ምን ያህል ሰው እንደሞተ፣ ስንት ጋብቻዎች እንደተፈፀሙና ስንቶቹ እንደፈረሱ የሚያመለክት መረጃ በቀጥታ አይገኙም። እነዚህ መረጃዎች ደግሞ የአሁኑንና የወደፊቱን የሕዝብ ብዛት ዕድገት ለማወቅ ወሳኝ መሠረት ናቸው። ስለዚህም እነዚህ ከሀገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማናቸውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዕቅዶች ዝግጅት ለማድረግ፣ ለአፈፃፀምና የአፈፃፀም ግምገማ አስፈላጊ የሆኑ የስነ-ህዝብ መረጃዎች በየዓመቱ አልፎም በአነሰ ጊዜ በጥራት መገኘት አለባቸው። በሌላም በኩል በሕዝብ ቆጠራና በናሙና ጥናት የሚገኙ መረጃዎች ለስታቲስቲክስና ለአስተዳደር አገልግሎት ብቻ ከመዋል ባሻገር የግለሰቦችን ሕጋዊ ሰውነትና ማንነት የሚገልጹ ሕጋዊ መረጃዎችን ለመስጠት አያገለግሉም።

በአንድ ህብረተሰብ ከኢኮኖሚው፣ ማህበራዊውና ፖለቲካዊው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መልኩ በግለሰቦችና በግለሰቦች፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች፣ በግለሰቦችና በመንግሥታዊ ተቋሞች፣ በግለሰቦችና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል ቀጥታ ግንኙነቶች በየዕለቱ ይፈፀማሉ። ለነዚህ ግንኙነቶች ተፈጻሚነት ደግሞ የግለሰቦችን ማንነትና ሕጋዊ ሰውነት የሚያረጋግጡ ሕጋዊ የኩነቶች ምስክር ወረቀቶች አስፈላጊ ናቸው። ምክንያቱም የኩነቶች መከሰትና የተዛማጅ መረጃዎች በህጋዊ ምስክር ወረቀቶች መደገፍ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊውና በፖለቲካው መስክ የሚነሱ የግልጋሎት ጥያቄዎችን በህጋዊና ዘመናዊ የህዝብ አስተዳደር አሰራር ለመመለስ ወሳኝ በመሆናቸው ነው። ኢትዮጵያ የተለያዩ የአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ሕጎችን ከተቀበሉት አገሮች አንዷ ናት። ይኸን በሚመለከት በአገራችን ሕገ-መንግሥትም ሆነ በዓለም አቀፍ ሕጎች የፀደቀውን የግለሰቦችን ሰብአዊ መብት ለማስጠበቅ የግለሰቦችን ማንነትና ሕጋዊ ሰውነት የሚገልፅ ህጋዊ መረጃ (ምስክር ወረቀት) ለእያንዳንዱ

ግለሰብ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ እነዚህን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች በአግባቡ ለመፈፀምና መተግበራቸውን ለመከታተል የሚያስችሉትን ዓለም አቀፍ አሠራሮች ለመተግበር መሣሪያ የሆኑትን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባ ሥርዓት እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ለመዘርጋት ተገቢውን ቀዳሚ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባታል።

በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነት ምዝገባዎችን ለማድረግ የሚዘጋጁ ህጋዊ የኩነት መከሰትና ተዛማጅ የግለሰብ ማንነት ገላጭ መረጃዎች ለግለሰቦች፣ ለማህበረሰቡና ለመንግሥት የሚያስገኙት ጥቅም በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይቶ ሊቀርብ ይችላል።

1 ለዜጎች የህግ ጥበቃ በመስጠትና መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን በማስጠበቅ፤
2. እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ድረስ ለሕዝብ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ ግለሰባዊ የሕግ መረጃዎችንና ለፖሊሲና ፕሮግራም ዝግጅት፣ አፈጻጸምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ መሠረት የሆኑ ቀጣይና ወቅታቸውን የጠበቁ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን ማስገኘት ናቸው።

በመሠረቱ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚገኙ መረጃዎች ሁለት ዓይነት ናቸው። እነርሱም ፦

ሀ. ግለሰባዊ የህግ መረጃዎችና
ለ. የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃዎች ናቸው። ከዚህም በላይ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለመስጠትና የግልጋሎት አሰጣጡን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የኩነቶችን መከሰት ከአድራሻ ዝርዝር ጋር የሚያሳዩ መረጃዎች ያስገኛሉ።

ከዚህ ቀጥሎ ስለሁለቱ ዋና ዋና የአገልግሎት ዘርፎች ማለትም ስለኩነቶች ምዝገባ መረጃዎች ጥቅምና አስፈላጊነት በዝርዝር ተመልክቷል።

1. ለዜጎች የህግ ጥበቃ በመስጠትና መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን በማስጠበቅ፣

ልደትና ሞት በሰው ልጅ ላይ የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊ ኩነቶች ሲሆኑ በሰው ልጅ ምድራዊ ህይወት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊከሰቱ የማይችሉ ተፈጥሮአዊ ኩነቶች ናቸው። ሰዎች በልደት አማካይነት ወደ ዓለም ህብረተሰብ አንድ ጊዜ ይቀላቀላሉ፤ በአንፃሩ ደግሞ በሞት አማካይነት ከዓለም አንድ ጊዜ ይለያሉ። በመሆኑም ልደትና ሞት በሰው ልጅ አፈጣጠርና አኗኗር የመነሻና የመድረሻ (ህይወትና ሞት) እርከኖችን ማሳያ/መለያ/ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው። በሌላም በኩል ጋብቻና ፍቺ ሰው "ህጋዊ ሰው" የመሆን መብት በሚያገኝበትና በሚያጣበት ማህበረሰባዊ የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ዋነኛ የሰዎች ማህበረሰባዊና ህጋዊ አቋም (Civil status) ለውጥ ጠቋሚ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው። እነዚህ በግለሰቦች ላይ የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊና ማህበረሰባዊ ለውጦች የአንድን አካባቢ (ሀገርም ሆነ አነስተኛ የአስተዳደር ክፍል) የህዝብ አስተዳደር በሥርዓት ለመምራት ለሚዘጋጁ ህጋዊና አስተዳደራዊ የአመራር ሥርዓቶች መነሻ መሠረቶች ናቸው። በመሆኑም ለምሳሌ የአንድ ሰው የመኖር ተፈጥሮአዊና ማህበረሰባዊ የህግ መብት መሰረቱ የሚጣለው ከተወለደበት/ችበት ቀን አንስቶ ነው። ስለሆነም ልደት በዚች ምድር የሰዎች የመኖር ህጋዊ መብት ምንጭ ኩነት በመሆኑ ማንኛውም ሰው በአንድ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ለመኖር ህጋዊ የዜግነት መብቱን የሚያገኝበትና ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነውን ህጋዊ ሰነድ የሚያዘጋጅበት የህይወቱ የመጀመሪያ እርከን ነው።

በጥቅሉ ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በመመሥረት ዓለም አቀፍ ዕውቅና ከተሰጣቸው መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። የመጀመሪያው ራሳቸው ወሳኝ ኩነቶቹ (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) የመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች አካል መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለበርካታ ዕውቅና ለተሰጣቸው መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መተግበር የአስተዳደር አፈፃፀም ሥርዓት ምንጭ መሆናቸው ነው። ይህንኑ መሰረት በማድረግ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ በአንድ በኩል የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ መመዝገብን በራሱ የሰብዓዊ መብት አድርጎ የደነገገው ሲሆን በሌላም በኩል እነዚህ ወሳኝ

ኩነቶች ለመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መተግበር የአስተዳደር አፈፃፀም ሥርዓት ምንጭ በመሆን የሚኖራቸውን ወሳኝ ድርሻ ለይቶ ያስቀምጣል። ይህንኑ የወሳኝ ኩነቶች መመዝገብና የሰብአዊ መብቶችን ቁርኝት መሠረት የጣለው እ.ኤ.አ. በ1974 የፀደቀው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የስነ-ህዝብ የድርጊት መርሀ-ግብር ሲሆን በዚህ መርሀ ግብር መሠረት መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች በሁለት ምድብ ተከፍለው ቀርበዋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል፦

## 1.1 የወሳኝ ኩነት የመመዝገብ መብትን መሰረት ያደረጉ

### 1.1.1 የልደት መመዝገብ መብት

- ዓለምአቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /24/
  - "Every child shall be registered immediatly after birth .... "
  - "ማንኛውም ህፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ መመዝገብ ይኖርበታል . . ."
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /7/
  - "The child shall be registered immediatly after birth and shall have the right to a name, the right to aquire a nationality, ..."
  - ህፃኑ ወዲያው እንደተወለደ የመመዝገብ፣ ስም የማግኘት መብት፣ ዜግነት የማግኘት መብት፣ . . . አለው።"
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ /36(ለ)(ሐ)/
  - ማንኛውም ህፃን ሥምና ዜግነት የማግኘት መብት አለው፣
  - ማንኛውም ህፃን ወላጆቹን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው፤
- የፍትሀ-ብሄር ህግ አንቀጽ 101 (1)
  - "የልጅ መወለድ በማናቸውም ሰው ለክብር መዝገብ ሹም መገለጽ አለበት፤"

እንደ ዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን መንግሥት በየዕለቱ በመወለድ የህብረተሰቡ አባል የሚሆኑ ሰዎችን የማህበረሰብ

አባልነታቸውን፣ ማንነታቸውን በሚለይ የምዝገባ አሰራር በቋሚ የመንግስት ሰነድ የመመዝገብ ግዴታ ተጥሎበታል፤ በዚህ ህጋዊ የመንግስት ሰነድ ላይ በመመሥረት ለተወለደው ህፃን ስለመወለዱና የማህበረሰቡ አባል ስለመሆኑ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትም ወዲያው እንደተወለደ መስጠት ይኖርበታል። ይህም አሠራር ዘመናዊና አግባባዊ የህዝብ አስተዳደር ሥርዓት መርህ ሆኖ ተቀምጧል። በነዚህ የምዝገባ ሰነዶች ላይ በመመሥረት መንግስት ለዜጎቹ ወቅቱን የጠበቀ የህግ፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና ልዩ ልዩ የአስተዳደር አገልግሎቶችን የመስጠትና የመቀበል ግዴታውን ይወጣል። በተመሳሳይ በዚህ ህጋዊ የልደት ምስክር ወረቀት አማካኝነት ህፃኑ በልጅነትና በቀሪ ዕድሜው የማህበረሰብ አባልነት መብቱን ለማስጠበቅና የዜግነት ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለው ህጋዊ መረጃ ይኖረዋል፤

1.1.2 የሞት መመዝገብ መብት

- ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /12/2 (a)/
  - the States parties must adopt, among other things, measurments aimed at "reduction of the still-birth rate and of infant mortality rate, ..."
  - የኮንቬንሽኑ አባል ሀገሮች ከሌሎች ተግባራት በተጨማሪ ቅድመ ወሊድ ሞትን እና የህፃናትን ሞት ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባቸዋል፤
- ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ /36(ሀ)/
  - ማንኛውም ህፃን በህይወት የመኖር መብት አለው።
- የፍትሀ-ብሄር ህግ አንቀጽ 105
  - የሞተን ሰው መሞቱን ማሳወቅና የመሞቱንም ጽሑፍ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፤

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ስለ ሞት መመዝገብ መብት በቀጥታ አይጠቅሱም። ነገር ግን የሞት መመዝገብ መብት የህፃናትን ጤናማ አስተዳደግ ከማስፈን ጋር በተያያዘ ተገልፖ ይገኛል። በሌላም በኩል ከሌሎች የሰብዓዊ መብቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ (ለምሳሌ ከመውረስ መብት፣ ከማህበራዊ ዋስትና ማስጠበቅ መብት፣ ...) የሞት መመዝገብ መብት አስፈላጊነት ተገልጿል።

መንግሥት ለግለሰቦችና ለአካባቢ አስተዳደር የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጣቸውን የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አገልግሎቶች አግባባዊውን አስተዳደር መሠረት አድርጎ ለመፈፀም በየዕለቱ በሞት ምክንያት ከህብረተሰቡ የሚለዩትን ሰዎች ከማህበረሰብ አባልነታቸውና ከመንግስት ሰነድ ለመሰረዝ የሞት ኩነት መመዝገብ ይኖርበታል። መንግሥት ይህንኑ የሞት መከሰት መረጃ የህግና የአስተዳደር አገልግሎት ሰጪ አካላት እንዲያውቁት ከማድረግ በተጨማሪ የሟች ዘመዶች ህጋዊ የሞት መከሰት ማረጋገጫ መረጃ እንዲሰጣቸው/እንዲኖራቸው/ ማስቻል ግዴታው ስለሆነ ሞት የመመዝገብ መብት እንዲኖረው ተደርጓል። በሌላም በኩል ስለአንድ ሀገር ወይም አካባቢ አስተዳደር የሞት መጠን ከነመንስኤው በማቀነባበር የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለማወቅና ተገቢውን የመከላከያ ዘዴ ለማዘጋጀት የሚረዳ መረጃ ለማጠናቀር ይህንኑ ኩነት መዝገቦ መያዝ ይኖርበታል።

1.1.3 የጋብቻ መመዝገብ መብት

- የጋብቻ ፈቃድ፣ የጋብቻ ዕድሜ እና የጋብቻ ምዝገባ ኮንቬንሽን አንቀጽ /3/፡
  - "All marriages shall be officially registered by the competent authority"
  - "ማንኛውም ጋብቻ የኩነቶች ምዝገባ እንዲያካሂድ ስልጣን ባለው የመንግሥት አካል መመዝገብ ይኖርበታል፤"
- በሴቶች ላይ የሚደረጉ ልዩነቶች ማስወገጃ ዲክላሬሽን አንቀጽ /6.3/፡
  - "effective action, including legislation, shall be taken to specify a minimum age for marriage and to make the registration of marriages in an official regsitry compulsory"
  - ትንሹን የጋብቻ ዕድሜ የሚወስንና ጋብቻን መንግሥት ባቋቋመው የጋብቻ መዝገብ ሥልጣን ባለው አካል ለመመዝገብ የሚያስገድድ ህግ እንዲወጣ መደረግ አለበት፤
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ /34(1)(2)/
  - በህግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች . . . የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው፤

- ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፤

➤ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ /28(1)(2)/

- ጋብቻው የተፈፀመው በማናቸውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም፣ አግባብ ባለው የክብር መዝገብ ሹም መመዝገብ አለበት፤
- ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

➤ የፍትሀ-ብሄር ህግ አንቀጽ 118

- ጋብቻው የተከበረው በምንም ዓይነት ፎርም ቢሆን አንድ የጋብቻ ማስታወቂያና የጋብቻ ጽሁፍ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፤

በየዕለቱ በጋብቻ የሚጣመሩ ጥንዶች በቤተሰብ ህጉ የተቀመጡ የጋብቻ አፈፃፀም ህጋዊ ሥርዓቶችን ተከትለው የተፈፀሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ጋብቻውን በመንግሥት ዕውቅና በመስጠትና ተጋቢዎቹም ህጋዊ አቋማቸው መቀየሩን በመንግሥት ሰነድ መመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት የህግ መርሆዎች ይገልጻሉ። የጋብቻ መከሰት የሚያረጋግጠውን ህጋዊ መረጃ ተጋቢዎች እንዲሰጣቸው/ እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ይህንኑ የማህበረሰብ አባልነት መብታቸውን ለማስጠበቅና ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ጋብቻ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል መመዝገብ እንዳለበት በአለም አቀፍ ድንጋጌዎች ላይም ተመልክቷል።

በኢትዮጵያ የጋብቻን መመዝገብ የሚደነግጉ አንቀፆች በፍትሀ-ብሄር ህጉና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተገልፆ ይገኛል፤ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት ላይም የጋብቻ መመዝገብን በቀጥታ የሚገልጽ አንቀጽ ባይጠቀስም፣ ለአፈፃፀማቸው ሲባል የጋብቻን መመዝገብ ግድ የሚያደርጉ መብቶች ተደንግገዋል።

### 1.1.4 የፍቺ መመዝገብ መብት

➤ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ 843(IX) 1954

- "A divorce or judicial separation shall be granted only by a competent judicial authority and shall be legally recorded ..."

- ፍቺ ወይም ህጋዊ መለያየት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት መወሰን ይገባዋል፣ በተጨማሪም ፍችው ህጋዊ ምዝገባ ይደረግለታል፤...

➢ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ /34(1)/

- በህግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች . . . በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፤

በየዕለቱ የሚፈርሱ ጋብቻዎች የተጋቢዎችን ህጋዊ አቋም ለውጥ የሚያስከትሉ ስለሆነ ይኸው ክስተት በመንግሥት እውቅና ተሰጥቶትና በመንግስት ሰነድ ተመዝግቦ ለመያዝ እንዲቻል፤ ይህንኑ የፍቺ መከሰት የሚያረጋግጠውን ህጋዊ መረጃ ተፋችዎች እንዲሰጣቸው/እንዲኖራቸው በማድረግ ተፋችዎችና ፍቺው የሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት በህጋዊ ሰነዱ የማህበረሰብ አባልነት መብታቸውን ለማስጠበቅ እንዲሁም ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል፣ ፍቺ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም የመመዝገብ መብት ይኖረዋል፤

1.2 በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ የሚገኙ ህጋዊ የኩነት መረጃዎች ለግለሰቦችና ለመንግሥት የሚያስገኙት የህግ፣ የአስተዳደርና የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ጥቅሞች፤

በማንኛውም የመብት እውቅና አሰጣጥና አቀባበል ሥርዓት ሁለት ዋነኛ ተዋናዮች ይኖራሉ። እነርሱም ባለመብቱና መብቱን በማወቅ/በመስጠት ግዴታ የተጣለበት አካል ናቸው። በማናቸውም የሰብአዊ መብት ማወቅ/መስጠትና ማክበር/ማስከበር ሂደት እነዚህ ሁለት አካላት ተለይተው መታወቅና ሀላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው መቆጣጠር በሚያስችል አሰራር ቁርኝት መፍጠር ይኖርባቸዋል። በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና ፍቺ ምዝገባ ህጋዊ መረጃዎች አማካይነት የሚጠበቁ የህግና የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ስምምነት ዶክመንቶች ከተካተቱት ጥቂቶቹን ከሀገሪቱ ህጎች ጋር በማዛመድ በአጭሩ ከታች ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡-

1.2.1 እያንዳንዱ ዜጋ በህጋዊ ስሙ ተለይቶ በመንግሥት ሰነድ የመታወቅ መብቱን በማረጋገጥ፤

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በቤተሰቡና በአካባቢው የሚለይበት ስም ሊኖረው እንደሚገባ ግልጽ ነው። ይኸም ተለምዶአዊ ስም የመስጠት ተግባር በልደት ጊዜ (ከልደት በኋላ) የሚፈፀም ቤተሰባዊ/ማህበረሰባዊ ተግባር ነው። ለተወለደው ልጅ በቤተሰቡና በአካባቢው ስም የመስጠት ተግባር ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ የመሆኑን ያህል ሁሉንም የሀገሪቱን ህዝብ በአስተዳደር ክልልና ክፍል ለይቶ የሚያስተዳድር መንግሥት የሚያስተዳድራቸውን ዜጎች ዕውቅና በመስጠት ረገድ የመጀመሪያው ተግባር እያንዳንዱን ዜጋ በስም ለይቶ በሰነዱ መያዝ ነው። ይኸንን የአንድ ሀገር የሕዝብ አስተዳደር አግባባዊና ዘመናዊ አሠራር በመከተል የምዝገባ ሥርዓቱን የዘረጉ ሀገሮች በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገር መንግሥታት ሲሆኑ በአንፃሩ በኢኮኖሚ ኋላ ቀር ሀገር መንግስታት ግን የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓታቸው ገና ከተለምዶአዊ አሰራር አልተላቀቀም።

በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች "ህፃናት ሥም የማግኘት መብት" እንዳላቸው የሚገልፁ አንቀጾች ተካተው ይገኛሉ። "ህፃናት ሥም የማግኘት መብት" አላቸው የሚለው አገላለጽ ስለአፈፃፀሙ ተገቢው ማብራሪያ ካልተሰጠው የተለያየ አተረጓጎም ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ አንፃር የድንጋጌው መነሻ መሰረት የህፃናቱ ወላጆች/ቤተሰቦች የሰጡትን ሥም መንግሥት በሰነዱ በቋሚነት የመመዝገብ ግዴታውን እንዲያሳዩ ተደርገው መደንገጋቸው ግልጽ ሊሆን ይገባል። በዚህ መብት አተገባበር የመብቱ ባለቤት የሚሆኑት ህፃናቱ ሲሆኑ መብቱን በማስፈፀም ግዴታ የተጣለባቸው ደግሞ የህፃናቱ ወላጆች/ቤተሰቦችና መንግሥት በጣምራ ናቸው። የማስፈፀም ግዴታ የተጣለባቸው የህፃናቱ ወላጆች/ቤተሰቦችና መንግሥት የግዴታቸው ዓይነትና መጠን በግልጽ ካልተቀመጠ የመብቱ አፈፃፀም ትልቅ እንቅፋት ይገጥመዋል። ስለሆነም በአንድ ሀገር የህፃናትን ሥም የማግኘት መብት ለመተግበር መነሻው መሠረት በልደት ጊዜ የመመዝገብ መብት ነው። በመሆኑም መንግሥት በሀገሩ የትኛውም የአስተዳደር ክፍል የተከሰቱ ልደቶችን የመመዝገብ ግዴታውን ለመወጣት የልደት አመዘጋገብ ሥርዓት ማበጀትና ተገቢውን

አስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት ያለበት ሲሆን ይኸንንም ቤተሰቦች እንዲያውቁት በማድረግ የልደት ምዝገባውን የማካሄድና ህጋዊ ማስረጃዎችን ለባለመብቱ (ለህፃናቱ) የመስጠት ግዴታውን የመወጣት ሀላፊነት አለበት። በዚህ ህጋዊ መረጃ ውስጥ የህፃናቱ ህጋዊ ስም እንዲሰፍር ይደረጋል።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ታሪክ በህገ-መንግስትና ልዩ ልዩ ህጎች የተካተተውን የህፃናትን ስም የማግኘት መብት ለማስከበር የሚያስችለው አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ሥርዓት በሚፈለገው መልክ ተግባራዊ አልተደረገም። በመሆኑም በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ የነበሩ መንግስታት የህፃናትን ሥም የማግኘት መብት እውቅናን ከመስጠት ያለፈ ህፃናቱን ባለ መብት አድርገው አያውቁም። በዚህም የትንሳ የኢትዮጵያ ህፃናት ገና የመብቱ ተጠቃሚ አልሆኑም ለማለት ይቻላል። ስለሆነም መብቱን በማወቅ/በመስጠትና በመተግበር የመጀመሪያውን ተግባር መፈፀም ያለበት መንግሥት ግዴታውን ሳይወጣ ቆይቷል። ይህም በመሆኑ ወላጆች/ቤተሰቦች መብቱን በማስፈፀም የሚኖርባቸውን የማስመዝገብ ግዴታ መወጣት ያለመወጣታቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም። ስለሆነም ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36(1) (ለ) - ማንኛውም ህፃን ስምና ዜግነት የማግኘት መብት እንዳለው በሚገልፀው አንቀፅ መሠረት የመብቱን ዕውቅና ያገኙትን ህፃናት የመብቱ ተጠቃሚ ለማድረግ በቀዳሚነት መንግሥት ግዴታውን ለማስፈጸም የሚያስችለውን የአፈፃፀም የህግና የአስተዳደር ሥርዓቶችን መዘርጋትና የልደት ምዝገባውን በመላ ሀገሪቱ መጀመር ይኖርበታል።

1.2.2 የህፃናት ወላጆች ማንነት በመንግሥት ሰነድ መታወቁ ልጆች ከወላጆቻቸው የሚፈልጉትን ግልጋሎት በማስጠበቅ የመብታቸው መከበር መሠረት ስለመሆኑ፤

እንደሚታወቀው የአንድ ሰው ስም የራሱንና የወላጆቹን ስም እንደሚያካትት ግልጽ ነው። ሰዎች በህፃንነት ዕድሜአቸው በወላጆቻቸው ልዩ ጥበቃ የማግኘት መብት ያላቸው ሲሆን ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን የማሳደግ ተፈጥሮአዊና ህጋዊ ግዴታ አለባቸው። በዚያው መጠን መንግሥት ይኸን የልጆችንና የወላጆችን ተፈጥሮአዊና ህጋዊ ግንኙነት

የማስጠበቅ አልፎም እንደማህበረሰብ አባልነታቸው ተገቢውን ጥበቃ የማድረግ ግዴታ አለበት። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ 36(ሐ) ላይ ህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና በወላጆቻቸው የመጠበቅ መብት እንደተሰጣቸው የሚገልጽ የህግ ዕውቅና ተደንግጓል። ሰዎች በተፈጥሮና ለዘመናት ባዳበሩት ባህላዊና የማህበራዊ አኗኗር ሥርዓት ያለምንም የጽሁፍ ህግ ወላጆች ለልጆቻቸው ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንደሚያደርጉ ይታወቃል/ይጠበቃል። ከላይ የተቀመጠው የመብት ዕውቅና የመስጠት ጉዳይ ዋና መነሻም ይኸንን ተፈጥሮአዊና ተለምዶአዊ አኗኗር መንግሥት በሰነዱ መዝግቦ በህጋዊ መረጃ እንዲደግፌው ለማድረግ ነው። በመሠረቱ ለዚህ መብት አፈፃፀም ዋናው መሰረት የልደት መመዝገብ መብት ነው። በልደት መዝገቡ አማካይነት መንግሥት የህፃናቱን ወላጆች ማንነት በሰነዱ ለመያዝ ስለሚያስችለው ዕውቅና የሰጠውንና ህፃናት ከወላጆቻቸው ተገቢው ጥበቃ ይደረግላቸው የሚለውን መብት መከበር ለመከታተልና ለማረጋገጥ ያስችለዋል፣ ከዚህም በላይ በወላጆቻቸው ተገቢውን እንክብካቤ የማያገኙ ህፃናትን መንግሥት በተጣለበት የመንከባከብ ግዴታ መሠረት መብታቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል። ስለሆነም መንግሥት እነዚህን ተያያዥ የመብትና ግዴታ ግንኙነቶች በሥርዓት ለመከታተልና ለማስፈጸም በሰነዱ ውስጥ የልጆችን ማንነት የሚገልጽ ህጋዊ መረጃ ሊይዝ ይገባል።

### 1.2.3 ማንኛውም ሰው በሀገሩ ህግ መሠረት ዜግነቱ በመንግሥቱ አስተዳደር የዜጎች ሰነድ ውስጥ በማያጠራጥር ሁኔታ ሲመዘገብና ሲታወቅለት የግድ ስለመሆኑ፣

በዓለም አቀፍ አግባባዊ የህዝብ አስተዳደር አሰራር መሠረት የአንድ ሰው ዜግነት በሁለት መንገድ ይሰጣል። እነርሱም በሀገሩ ድንበር ውስጥ በመወለዱ ወይም በወላጆች ዜግነት ላይ በመመሥረት ይሆናል። በተጨማሪም በአስተዳደራዊ መንገድ በጋብቻ፣ ዜግነትን በመቀየርና በመሳሰሉ ምክንያቶች ዜግነት ሊገኝ ይችላል። ይህ የዜግነት አሰጣጥ አፈፃፀም የሀገሩ የዜግነት ህግ በሚደነግገው መሠረት ይወሰናል። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ማንኛውም ሰው እንደተወለደ ዜግነት ሊያገኝ እንደሚገባ የዓለም አቀፍ ስምምነት ያዛል። የሰዎች የዜግነት ማንነት የሚረጋገጠውም በልደት ምዝገባ አማካይነት እንዲሆን ይኸው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሰነድ ይገልፃል። በሀገራችን ህገ-መንግሥት አንቀጽ 36(1) (ለ) ማንኛውም ህፃን

ዜግነት የማግኘት መብት እንዳለው ከመደንገጉም በላይ ይኸው አንቀጽ ሰዎች ሁሉ ዜግነታቸው በመንግሥት ሰነድ ሊታወቅ የሚገባው እንደተወለዱ መሆኑን ያመለክታል። በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ (6/1) "ወላጆቹ/ወላጆቿ ወይም ከወላጆቹ/ከወላጆቿ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ ነው/ናት" በማለት በኢትዮጵያ የዜግነት አሰጣጥ ሥርዓት በትወልድ ሀረግ ላይ እንደሚመሠረት ደንግጓል። በሌላ አገላለጽ በኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት መሠረት ለህፃናትም ሆነ ለአዋቂዎች ዜግነትን ለመለየት መነሻው የወላጆች ዜግነት ነው። ከላይ ስለ ህፃናት ስም የማግኘት፣ ወላጆቻቸውን የማወቅና በወላጆቻቸው የመጠበቅ መብት ስናነሳ ለነዚህ መብቶች መከበር መሠረቱ የልደት መመዝገብ መብት መሆኑም በተጨማሪ ተመልክቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የዜግነት መብት አፈፃፀም አስተዳደራዊ ሥርዓት አዘረጋግ መነሻው የልደት መመዝገብ መብት ተግባራዊ መሆን ነው። በርግጥ ከዚህም በላይ የወላጆች ዜግነት ለህፃናቱ ዜግነት ውሳኔ አሰጣጥ መሠረት ስለሆነ የወላጆች ህጋዊ የልደት መዝገብ መረጃ መኖር በኢትዮጵያ በዜግነት ሰነድ ዝግጅት ሒደት ውስጥ አስፈላጊ ነው።

1.2.4 ልጆችን ከልጅነት ጋብቻ ስመከላከልና ያስዕድሜአቸው ጋብቻ እንዲፈጽሙ ከተገደዱ በህግ ፊት መብታቸውን ስማስጠበቅ መሠረታዊው ዋስትና የልደት መዝገብ ስስመሆኑ፣

በተለያዩ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ህፃናት ከልጅነት ጋብቻ መጠበቅ እንዳለባቸው ተመልክቷል። በሀገራችንም የጋብቻ ዕድሜ በኢትዮጵያ ፍትሀ-ብሔር ህግም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተደንግጎ ይገኛል። በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ (7/1) "ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም አይችሉም፤" በሚል ተደንግጓል። በርግጥ ይህ አንቀጽ ትንሹን የጋብቻ ዕድሜ የህግ ዕውቅና ይሰጣል፣ ይሁን እንጂ እንደሌሎች መብቶች ሁሉ የመብቱ ባለቤት የሆኑት ህፃናት ራሳቸውን ከልጅነት ጋብቻ ለመጠበቅ የሚያስችላቸው ህጋዊ መረጃ እንዲኖራቸው የሚያደርግና፣ እንዲሁም መንግሥት የነዚህ የህፃናት መብት እንዳይደፈር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያበቃውን አግባባዊ አስተዳደራዊ መሠረት አልጣለም። ስለዚህ ይህን የገባውን ግዴታ የሚጠብቅበትና መጠበቁን የሚያረጋግጥበት አግባባዊ አስተዳደራዊ

አሠራር መዘርጋት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የህፃናቱ ቤተሰብም ሆነ ማህበረሰቡ ህፃናት በህግ በተደነገገላቸው የጋብቻ ዕድሜ ላይ ሳይደርሱ ለማግባት እንዳይገደዱ የሚጠብቃቸውንና መንግሥትም ይህንኑ ለማረጋገጥ እንደመረጃ የሚገለገልበትን የልደት የምዝገባ ሰነድ ማለትም ህፃናቱ በተወለዱ ጊዜ ተመዝገቦ የተያዘ ዝርዝርና ህጋዊ የልደት መዝገብ እንዲኖር አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በኢትዮጵያ በተለይ በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ዕድሜአቸው ለጋብቻ ያልደረሱ ልጆችን የመዳር ልማዳዊ ሥርዓት የተለያዩ ባህላዊ ወጎችን በመከተል አሁንም ድረስ ይከናወናል። በዚህ በኩል ዕድሜአቸው ለጋብቻ ያልደረሱ ልጆችን የሚድሩ ዜጎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ለማድረግ በቅድሚያ ህጉን ለመጣስ በምክንያትነት የሚያቀርቡትን ቀዳዳ መድፈንን ይጠይቃል። በየአካባቢው እንደሚታየው ልጆችን ለመዳር የሚፈልጉ ወላጆች የልጆቹ ዕድሜ ለጋብቻ ሳይደርስ ደርሷል በማለት በሰው ምስክር በተገመተ ዕድሜ ጋብቻው እንዲፈፀም ለማድረግ ይሞክራሉ። በሌላም በኩል ጋብቻውን ከፈፀሙ በኋላ የልጁ/የልጅቷ ዕድሜ ለጋብቻ የደረሰ መሆኑን በህግ ፊት ጭምር ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ። የዚህ ችግር መንስኤ ህፃናት እንደተወለዱ በልደት መዝገብ ያለመመዝገባቸውና በህፃናቱ እጅም ሆነ በመንግሥት ሰነድ የልደት ቀን መረጃ ያለመኖር በመሆኑ ህፃናትን ከልጅነት ጋብቻ የመጠበቅን መብት ለማስጠበቅ ዋነኛው የህግ አፈፃፀም መሣሪያ የልደት ምዝገባ ሥርዓትን በሀገሪቱ እንዲቋቋም በማድረግ የማንኛውም ህፃን የልደት ቀን በመንግሥት ሰነድ እንዲያዝና እንዲታወቅ ማድረግ ነው።

1.2.5 ወጣት አጥፊዎች በትክክለኛ ዕድሜአቸው ላይ የተመሠረተ ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግና እነሱን በተመለከተ የተሰጠውን የሰብዓዊ መብት እውቅና ለማስጠበቅ በዋነኝነት የመብት ማስጠበቂያው መሣሪያ ልጆች እንደተወለዱ በመንግስት ሰነድ (በልደት መዝገብ) እንዲመዘገቡ ማድረግ ስለመሆኑ፤

ከልደት መዝገብ የሚገኘው አንዱና መሠረታዊው መረጃ የግለሰቦችን ትክክለኛ ዕድሜ ለማስላት የሚያስችለው ህጋዊ የልደት ቀን መረጃ ነው። እንደሚታወቀው በተለያየ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ዜጎች ልዩ ልዩ ዓይነት ከባድና ቀላል ጥፋቶችን ይፈጽማሉ። እንደሌሎች ሀገሮች ሁሉ በሀገራችንም የወንጀለኛና የፍትሀ-ብሄር ህግ ለወጣት አጥፊዎች የሚሰጠውን የፍትህ ሥርዓት ከአዋቂዎች ለይቶ ደንግጓል። በዳኝነት

ስርዓቱ አንድን ጥፋተኛ ወጣት ወይም ጎልማሳ ነው ብሎ ለማረጋገጥ የሚጠየቀው የመጀመሪያው የመረጃ መሠረት በሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ከተዘጋጀ ህጋዊ የልደት መዝገብ ላይ የተመሠረተ የልደት ምስክር ወረቀት እንዲቀርብ ነው። ህጋዊ የልደት ምስክር ወረቀት በሌለበት በእንደኛ ዓይነት ሀገር በምንም መልኩ ህጉን የተከተለ ፍትህ በወጣት አጥፊዎቹ ላይ መውሰድም ሆነ ወጣት አጥፊዎችን የሚመለከቱ ሰብዓዊ መብቶችን በአግባቡ መተግበር አይቻልም። የነዚህን መብቶች ማስፈፀሚያ የአስተዳደር ሥርዓት ባልዘረጉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች በህፃናቱ ላይ የሚደርሰውን ይህን ጉዳት ወይም በቤተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የፍትህ መዛባትና መጓተት መገመት አያዳግትም። በዚህ ረገድ በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ (36/3) "ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ... ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው" በሚል የተደነገጉ መብቶችንና በቤተሰብ ህጉ አካለ መጠን ስላልደረሱ ልጆች የሚመለከቱትን የህግ አንቀጾች ወደ ተግባር ለማምጣትና ተገቢውን ፍትህ ለመስጠት የልደት መመዝገብ መብትን መንግሥት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል።

1.2.6 በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ ወይም ጋብቻው ሲፈርስ የሚከሰቱ የመብት መጣሶችን ስመከላከልና ተገቢውን ፍትሃዊ የአስተዳደርና የህግ ውሳኔ በአፋጣኝ ለማድረግ ጋብቻው በመንግሥት ዕውቅና አግኝቶ መመዝገቡ የችግሮች መፍቻ ቁልፍ ስለመሆኑ፤

ለመልካም ትዳር የተጋቢዎች መተሳሰብና መተማመን ዋነኛው መሠረት ቢሆንም ጋብቻው በመንግሥት ዕውቅና አግኝቶ በሰነድ መመዝገቡ ተጋቢዎች በትዳራቸው እኩል መብታቸውን በማስጠበቅ ረገድ ትልቁ ዋስትና ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በተለያየ ጊዜ በወጡ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት አካል በሆኑ ድንጋጌዎች ጋብቻ አግባብ ባለው መንግስታዊ አካል መመዝገብ እንዳለበት ተመልክቷል። የጋብቻ መመዝገብ መብትን በተመለከተ እንደ ልደት መመዝገብ መብት ሁሉ የመብቱ ባለቤቶችንና መብቱን የማወቅና/የመስጠትና የማስከበር ግዴታ ያለባቸውን አካላት መለየትና ሀላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ለመቆጣጠር በሚያስችል የአሰራር ስልት ማስተሳሰርን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ የመብቱ ባለቤቶች ተጋቢዎችና ቤተሰባቸው ሲሆኑ መብቱን ለባለመብቶቹ

የመስጠትና የማስከበር ሀላፊነት ደግሞ የመንግሥት ነው። እዚህ ላይ ተጋቢዎች መንግሥት ባዘጋጀላቸው የአመዘጋገብ ሥርዓትና የምዝገባ ህግ በመመራት የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን የዚህ ግዴታ ምንጭና ጠቀሜታ ወደፊት ልጆቻቸው የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻሉ ጭምር ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በልዩ ልዩ ህጎች የተደነገጉና በቤተሰብ ጥበቃ ላይ የተመሰረቱ መብቶችን አፈፃፀም ለማረጋገጥ የሚቻለው አስቀድሞ ጋብቻው በመንግሥት ዕውቅና ሲያገኝና በጋብቻ መዝገብ ሲመዘገብ ብቻ ነው። ጋብቻው እንደተፈፀመ ወይም ጋብቻው ሲፈፀም በመንግስት ሰነድ መመዝገቡ የጋብቻውን ህጋዊነት ከመነሻው የማረጋገጥ መሠረቱን ይጥላል። ይህ በመሆኑም በጋብቻው ላይ የሚነሱ የህጋዊነት ጥያቄዎች በሙሉ ከመነሻው ዕልባት አግኝተዋል ለማለት ያስችላል። በሌላ በኩል ከጋብቻ አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ችግሮች የሚነሱት ጋብቻው በፍቺ እንዲለይ በሚፈለግበት ወቅት ነው። በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ፍቺ ለማድረግ ሲፈለግ ጋብቻው አስቀድሞ በህግ ዕውቅና ያልተሰጠው ከሆነ ህጋዊ አሠራሮችን ተከትሎ መፍትሄ ለመስጠት የመረጃ ችግሮች ይከሰታሉ። ጋብቻ በመንግሥት ዕውቅና አግኝቶ ባለመመዝገቡ ምክንያት በሚከሰቱ ችግሮች ዋንኛ ተጠቂዎችም እናቶችና ህፃናት ናቸው። ስለዚህ መንግሥት ያወጣቸውን የህግ ሥርዓቶችንና የመብት ጥበቃዎችን ደረጃ በደረጃ ለማስፈፀም የጋብቻ ምዝገባ ሥርዓቱን ማቋቋም ቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን ይገባል።

1.2.7 ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በእድሚአቸው እንዲጀምሩና መንግሥትም እያንዳንዱ ህፃን ይኸ መብቱ መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን መረጃ በመንግሥት ሰነድ ተመዝግቦ/ተዘጋጅቶ እንዲገኝ ማድረግ ስለማስፈለጉ፤

ህፃናት ከተወለዱ ጀምሮ በዋንኛነት ከቤተሰባቸውና ከመንግስት ሊያገኙ የሚገባቸው መሠረታዊ አገልግሎት የጤና ክብካቤና ተገቢው የቤተሰብና የማህበረሰብ ፍቅር እንዲሁም ጥሩ የመኖሪያ አካባቢ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ በቤተሰቡና በመንግሥት በኩል ከተወለዱ ጀምሮ በዕቅድ ተይዞ ትምህርት ቤት ለመግባት በሚያስችል ዕድሜ ላይ ሲደርሱ ትምህርት

የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ተገቢው የትምህርት ተቋም በአካባቢያቸው እንዲቋቋም ማድረግ፣ ለህፃናቱም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንዲቀርቡ ማገዝና በቤት ውስጥም ትምህርታቸውን በሚገባ ለመከታተል የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች፣ አልባሳትና ምግብ መቅረባቸውን ማረጋገጥ ይገባል። እነዚህን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ህፃናት በራሳቸው ሊያደርጉት የሚችሉት ተግባር ባለመኖሩ ዕድሜአቸው ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ ተገቢው ሁሉ በወላጆቻቸው፣ በህብረተሰቡና በመንግሥት ሊደረግላቸው የግድ ነው። በመርህ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነፃ ለህፃናት መቅረብ እንዳለበት በአመዛኙ የዓለም ክፍል ተቀባይነት ያገኘና እየተተገበረ ያለ የሰብዓዊ መብት አካል ነው። በዚህም ወላጆችና መንግሥት የህፃናትን ትምህርት የማግኘት መብት በማስጠበቅ ግዴታውን በጋራ ተቀብለዋል። ይኸውም ወላጆች መንግሥት በሚያዘጋጀው አጠቃላይና አካባቢያዊ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ዝግጅት የሚፈለግባቸውን ድጋፍ በመስጠት ይሳተፋሉ፤ በተጨማሪም ለልጆቻቸው የትምህርት ዝግጅት አስፈላጊ ግላዊ ቁሳቁሶችን ያሟላሉ፤ ከዚህም በላይ ልጆቻቸው መንግሥት ባዘጋጀው የትምህርት ተቋማት በወቅቱ እንዲገቡና ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋሉ። ከወላጆች የሚጠበቀውን ይህን የመብት ማስጠበቅ ዝግጅት ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት ተቋማቱን በህፃናቱ የመኖሪያ አካባቢ በመክፈት፣ ተገቢውን ቁሳቁስና የሰው ኃይል በማቅረብና በማዘጋጀት መብቱን ለማስጠበቅ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይጠበቅበታል።

1.2.8 ህፃናት ከተወለዱ ጀምሮ ከእናታቸውና ከቤተሰቡ ሊያገኙ የሚገባቸውን እንክብካቤ እያገኙ መሆናቸውን መንግሥት የመከታተልና የመቆጣጠር ሀላፊነትን ስመወጣት እንዲያስችለው የህፃናቱን መወለድ በመንግሥት ሰነድ መመዝገብ የመብት ማስፈጸሚያ ስልት ስለመሆኑ፤

ህፃናት በአእምሮአቸውና በአካላቸው የጎለበቱና በቀጣይም ጤናማ አስተዳደግ እንዲኖራቸው በማድረግ ቅድሚያ ኃላፊነቱን የሚወስደው ወላጅ/ቤተሰብ ሲሆን፤ በአንፃሩ ህፃናቱ ከወላጆቻቸው ተገቢውን ጥበቃ እያገኙ መሆኑን ማረጋገጥና አልፎም ከወላጆቻቸው አቅም በላይ የሆነውን ማሟላት የመንግሥት ተግባር ነው። እንደሚታወቀው አንድ ህፃን ቢቻል ከመወለዱ በፊት ጀምሮ በእናቱ አማካይነት ተገቢውን የጤና እንክብካቤ

ማግኘት ይኖርበታል። ቀጥሎም በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱ ህጋዊ መረጃ አማካይነት ልዩ ልዩ የሰብአዊ መብት ማስጠበቂያ ህጋዊ መረጃ መስጠትና ጥበቃው ከህፃናቱ የትውልድ ዕለት መጀመር ይገባዋል። በመርህ ደረጃ የህፃኑን/ኗን መወለድ ከቤተሰቡ ቀጥሎ ማወቅ ያለበት መንግሥት ነው። ኢኮኖሚያቸው በበለፀጉ ሀገሮች ወሊድ በጠቅላላው በጤና ማዕከላት የሚፈፀም በመሆኑ ይህ መርህ ህፃናቱ እንደተወለዱ ወዲያው ተግባራዊ ይሆናል። በአንፃሩ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በኢኮኖሚ ኋላቀር ሀገሮች ግን አብዛኛው ወሊድ የሚፈፀመው በቤት ውስጥ ስለሆነ መንግሥት የህፃናቱን መወለድ የሚያውቅበት ሥርዓት ካልተበጀ በስተቀር ከወላጆች ቀጥሎ የመወለዱን ኩነት ሊያውቅና በዚያም ላይ ተመሥርቶ የመብት ጥበቃውን ሊያደርግ አይችልም።

እንደሚታወቀው ህፃናት እንደተወለዱና ከወሊድ በኋላ ወቅቱን (ዕድሜአቸውን) የተከተለ በቅድሚያ ልዩ ልዩ የበሽታ መከላከያ መድሃኒቶችን (ክትባት) ማግኘት ይኖርባቸዋል። የህፃናት ጤንነት መጠበቅ መብትን ዕውን ማድረጊያው ይኸ ህፃናትን ከልዩ ልዩ በሽታዎች ለመከላከል የሚያስችሉ መድሃኒቶችን በክትባትና መሳይ የህክምና አሰጣጥ ሥርዓት ወቅቱን እየጠበቁ እንዲያገኙ ማድረግ የመንግሥት ቀዳሚው ተግባር ነው። የህፃናት ሞት ምጥንትን ለመቀነስም መቆጣጠሪያው ዋነኛ መሣሪያ ይኸው የክትባት አገልግሎት ነው። ይኸን መብት በማስጠበቅ በኩል የህፃናቱ ወላጆች ግዴታውን በመቀበል ተቀዳሚ ኃላፊነት የሚወስዱ ሲሆን በዚያው መጠን መንግሥት ቤተሰቡን በመደገፍና በተለያየ ምክንያት ግዴታውን ያልተወጣውን ቤተሰብ ኃላፊነት በመቀበል የህፃናቱን ጤንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት። ይህንን ግዴታውን ለመወጣት የህፃናቱን መወለድ ማወቅና በሰነዱ በመመዝገብ፣ መረጃውን መሠረት ያደረገና ዕድሜአቸውን የተከተለ የበሽታ መከላከያና ሌሎች የጤና ክብካቤዎችን ማድረግ ይጠበቅበታል።

2.2.9 በአንድ ሀገር በየዕለቱ የሚከሰቱ የህፃናትም ሆነ የአዋቂ ሰዎችን ሞት ከነምክንያቱ ጥምር በመመዝገብ መንግሥት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የሞት መጠን የመቀነስ ሀላፊነቱን ስመወጣት እንዲችል የሞት መከሰትን በመንግሥት ሰነድ መመዝገብ ስለማስፈለጉ፣

በአንድ ሰው ላይ የሚደርስ የሞት መከሰት በቀሪ ዘመዶቹ፣ በማህበረሰቡና በመንግስት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በዋነኛነት በሟች ዕድሜ ላይ ይመሠረታል። በኢኮኖሚ በበለፀጉ ሀገሮች አማካይ የሞት ዕድሜ ከ75 ዓመት በላይ ሆኗል። ይኸም ማለት ሰዎች በጎልማሳነት ዕድሜአቸው ለቤተሰባቸውና ለሀገራቸው ሊያበረክቱ የሚገባቸውን አገልግሎት በማጠናቀቅ የሞት ዕድሜ ላይ እንደሚደርሱ ያመለክታል። በአንፃሩ በታዳጊ ሀገሮች የሰዎች አማካይ የሞት ዕድሜ ከ45 እስከ 55 እንደሆነ በጥናቶች ተመልክቷል። ይኸም የሚያሳየው አብዛኛው ሰው ለሀገሪቱ ማገልገል የሚገባውን ያህል ዕድሜ ሳይቆይ እንደሚሞት ነው። ስለሆነም በታዳጊ ሀገሮች የሚታየው የሞት ምጥነት ስርጭት ለሀገሪቱ ልማትና ዕድገት ትልቅ እንቅፋት ነው።

ሰዎች በእርጅና ምክንያት መሞታቸው የማይቀር የተፈጥሮ ህግ ቢሆንም በዕድሜ ሳይሆን በህክምና ለመከላከል በሚቻሉ በሽታዎች ምክንያት በርካታ የታዳጊ ሀገር ዜጎች ያለጊዜ ሕይወታቸው ያልፋል። ለምሳሌ በታዳጊ ሀገሮች በወሊድ መወሳሰብ ምክንያት በበርካታ እናቶችና ህፃናት ላይ ሞት ይከሰታል። ከወሊድ በኋላም በተለይ ህፃናት ተገቢውን የበሽታ መከላከያ መድሃኒት ባለመውሰዳቸው ህይወታቸው ይልፋል። በኢትዮጵያና መሰል ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ በተላላፊ የህፃናት በሽታዎች ምክንያት በርካታ ህፃናት ዕድሜአቸው አምስት ዓመት ሳይሞላ ይሞታሉ። ለሞታቸው መከሰት መንስኤ የሆኑት የተለያዩ በሽታዎች መድሀኒት ያላቸው መሆናቸው ከታወቀ ደግሞ ለሞት መንስኤ የሆኑትን በሽታዎች እንዳይከሰቱ መከላከልና ህፃናቱን ማትረፍ ተገቢው አካሄድ ነው። በዚህ ረገድ ግለሰቦች ሕመም ሲሰማቸው በተገቢው ጊዜ ወደ ህክምና ተቋም በመሄድ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል የህክምና ተቋማቱን ለማህበረሰቡ ቅርብ በሆነ አካባቢ ማቋቋም አንዱ መንገድ ነው። እንደሚታወቀው የበሽታዎች ዓይነትና ስርጭት ከአካባቢ መልክዓ ምድርና ከማህበረሰብ አኗኗር ጋር ቀጥታ ቁርኝት ስላለው እነዚህን የጤና

አገልግሎት ተቋማት በተገቢው ቦታ ለማቋቋምና የጤና ችግሮቹን መሠረት ባደረገ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የህክምና አገልግሎቱን ለማቅረብ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የበሽታዎችን ዓይነትና ስርጭት የሚያሳይ መረጃ ማጠናቀርን ይጠይቃል።

እዚህ ላይ ይህን ማህበራዊ ችግር ለመቅረፍ ሁለት ዓይነት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች ሊታሰቡ ይችላሉ፣ አንደኛው በሽታዎች ከመከሰታቸው አስቀድሞ እርምጃ መውሰድ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሽታው ሲከሰት የህክምናውን አገልግሎት ለበሽተኛው መስጠት ነው። እነዚህን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ ሁለት ዓይነት መረጃዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን ከእነዚህም የመጀመሪያው ግለሰባዊ መረጃዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን ግለሰባዊ መረጃዎች በማጠናቀር የሚገኘው የስታቲስቲክስ መረጃ ነው። በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የግለሰቦች ጤንነት መብት የመጠበቅ መለኪያ አንዱ መንገድ የሞት መጠንን መቀነስ ነው። በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነት ዶክመንቶች ላይ በተለይም የእናቶችንና የህፃናትን ጤንነት በመጠበቅ በኩል እንደ መብት ማረጋገጫ ተደርጎ የተቀመጠውን መንገድ በአግባቡ ለመተግበር እንዲቻል ከተፈለገ ከሞት ምጥንት መረጃ በተጨማሪ ለሞት መንስኤ የሆኑ በሽታዎችን መረጃ ማጠናቀር የግድ ይላል። እነዚህ የመብት ማስጠበቅ መሠረት የሆኑት የሞት ምክንያት መረጃዎች በአግባባዊ መረጃ አጠነቃቀር አሠራር የሚገኙት ህጋዊ የሞት ምዝገባ ሥርዓትን በሀገሪቱ በመዘርጋት ብቻ ነው። ስለሆነም የሞት ምክንያት መረጃ በሞት መዝገብ ላይ የሚካተት ስለሚሆን የጤና አቅርቦትና አገልግሎት ሥርዓቱን በአግባባዊ የሕዝብ የአስተዳደር ምሪት ለማስተዳደር ያስችላል።

1.2.10 እንድ ግለሰብ በመሞቱ ምክንያት ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ የሚደረጉ የንብረት ውርስ ጥያቄዎችን በህግ ፊት አፋጣኝ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን መንግሥት በሰነዱ ይዞ እንዲቀይ ስለማስቻሉ፣

ሰዎች ንብረት የማፍራት ህጋዊ የዕድሜ ደረጃ ላይ ከደረሱ በኋላ በሚሞቱበት ጊዜ በህይወት ዘመናቸው ያፈሩትን ጥሪት ለቀሪ ዘመዶቻቸው የማውረስ ልማድ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው። ይህንኑ ልማድ ህጋዊ ድጋፍ ለመስጠት በፍትሀ-ብሄር ህጎች በሞት ምክንያት የሚደረጉ ንብረት

የማውረስ ሥርዓቶች ተደንግገው ይገኛሉ። እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች በመከተል የውርሱን ሥርዓት ለማስፈፀም ወራሾች ለሟች ያላቸው ህጋዊ የዝምድና ዓይነትና የዕድሜ መረጃ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች የመውረስ መብት ማስጠበቂያ የአስተዳደር አፈፃፀም መሳሪያዎች እንደሆኑ በልዩ ልዩ ሰነዶች ውስጥ ተካቶ ይገኛል። ይህንን መብት ዕውቅና ከመስጠት ባሻገር ባለመብቱንና መብቱን በማስጠበቅ ግዴታ የተጣለበትን አካል በአስተዳደራዊ አፈፃፀም ሥርዓት የሚያቆራኛቸውን አሠራር ማወቅ ተገቢ ነው። የመብቱ ባለቤት የሆኑ የሟች ዘመዶች ሞቱ ስለመከሰቱ የሚያረጋግጥ የሞት መከሰት መረጃ በሞት ምዝገባ አማካይነት በመንግስት ወዲያው ሞቱ እንደተከሰተ ሊሰጣቸው ይገባል። ከዚህም በላይ የሞት መከሰት መረጃውን የተሟላ የሚያደርጉት የዝምድናና የዕድሜ መረጃዎች ቀደም ሲል ሟች ሲወለድ በመንግስት ሰነድ በተመዘገበ የልደት መረጃ መያዝ ይኖርበታል። በነዚህ የሟች የልደት ምዝገባና የሞት ምዝገባ ህጋዊ መረጃዎች ዋቢነት የመውረስ መብትን በፍርድ ቤቶችም ሆነ በማናቸውም የአስተዳደር ቦታ ያለ ስስተኛ ወገን አስረጅነት ማስጠበቅ ይቻላል።

1.2.11 የአንድ ሀገር ዜጎች ወደ ውጭ ሀገር ለመጓጓዝ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የጉዞ ሰነዶች በዋነኝነት ፓስፖርት ለማዘጋጀት የዜጎችን ማንነት የሚገልጽ መረጃ በመንግስት ሰነድ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ለማድረግ ስለማስቻሉ፤

ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከሀገራቸው ወደተቀረው የዓለም ክፍል በየዕለቱ መንቀሳቀሳቸው ግልጽ ነው። ባለንበት ዘመን ሰዎች ከሀገር ሀገር በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ማንነታቸውን የሚገልጽ የጉዞ ሰነድ (መታወቂያ) በመሆን በሀገሮች ስምምነት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው ፓስፖርት ነው። ፓስፖርት ስለመንገደኛው ማንነት በተለይ ዜግነቱንና የመንቀሳቀስ ፍቃዱን የሚያመለክቱ ህጋዊ መረጃዎች እንዲይዝ ተደርጎ ይዘጋጃል። በመሠረቱ ፓስፖርት ሰዎች ከሀገራቸው ውጪ ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸውና በመንግስታቸው የሚሰጣቸው ህጋዊ የጉዞ ሰነድ/መረጃ ነው። በዚህ በኩል በሁሉም የዓለም ክፍል ከሀገር ሀገር ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የፓስፖርት አሠራር ተቀባይነት አግኝቶ ከበርካታ አመታት ጀምሮ እየተሠራበት ይገኛል። ይህ ህጋዊ መረጃ ሰዎች ከሚነሱበትና ከሚሄዱበት ሀገር ደህንነት አንፃር አልፎም የግለሰቡን

ህጋዊነት ከማረጋገጥ አኳያ ትልቅ ጥንቃቄ በማድረግ መዘጋጀት የሚገባው ሰነድ ነው። በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ውስጥ ማንኛውም ሰው የመዘዋወር ነፃነቱ መጠበቅ እንዳለበት ተደንግጎ ይገኛል። በርካታ ሀገሮችም ይህን መብት ተቀብለው ይጠቀሙበታል። በመሠረቱ ለፓስፖርት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የማንነት መረጃዎች ለምሳሌ ህጋዊ ስምና ዜግነት እንዲሁም የትውልድ ዘመንና የትውልድ ቦታ መረጃዎች በአግባባዊ አሠራር መገኘት ያለባቸው ከህጋዊ የልደት ምዝገባ መረጃ ነው። ይህ የመረጃ ሥርዓት በሌለበት ሀገር የሰዎች ያልተገደበ የመዘዋወር ነፃነት ተጠብቋል ለማለት አይቻልም። በመሠረቱ እነዚህን ግለሰባዊ የማንነት መረጃዎች የያዘ ሰነድ ማናቸውም በአንድ ሀገር አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖር ሰው ከተወለደ ጥቂት ቀናት በኋላ በልደት ምስክር ወረቀት መልክ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን በተመሳሳይ እነዚህን ግለሰባዊ የማንነት መረጃዎች መንግስት ያ ሰው ከተወለደ ጥቂት ቀናት በኋላ በሰነዱ ሊይዛቸው የሚገቡ መረጃዎች ናቸው። በኢትዮጵያ ያለው የዜጐች የፓስፖርት ዝግጅትና አሰጣጥ በዚህ አግባባዊና ዘመናዊ ህጋዊ የማንነት መረጃዎች አቅርቦት ሥርዓት ላይ በመመሥረት እየተከናወነ ያለ አይደለም። ስለሆነም በተለይ የልደት ምዝገባ ሥርዓቱ በሀገሪቱ መቋቋም እነዚህንና መሰል የአስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ አሠራሮችን ወደ አግባባዊና ዘመናዊ የሕዝብ አስተዳደር አሠራር በመሸጋገር ዕውቅና የተሰጣቸውን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን በማናቸውም የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ መከበራቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል።

1.2.12 የመምረጥና የመመረጥ መብትን ለመጠቀም የእያንዳንዱ ግለሰብ የዕድሜ፣ የዜግነትና ተመሳሳይ የማንነት መረጃዎች በመንግሥት ሰነድ ተመዝግበው እንዲገኙ ለማድረግ እንዲቻል፣

በመንግሥት የህዝብ አስተዳደርና አደረጃጀት አወቃቀር ሕዝቦች የውክልና ፈቃዳቸውን የሚሰጡበት ሥርዓት ግለሰብን መሠረት ባደረገ የምርጫ ሒደት ተወካዮቻቸውን በመምረጥ ይከናወናል። ይህ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት በሀገሪቱ መንግስት የህግ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት ለዜጎች ዕውቅና ይሰጣል። የምርጫ ሥርዓት አፈፃፀም በተለያዩ ሀገሮች የተለያየ አሠራር ሊከተል ቢችልም የጋራ የሆኑ የምርጫ ሥርዓት መርሆዎች አሉት። እነዚህ የምርጫ አፈፃፀም መርሆዎች በአግባባዊ

የግለሰቦች ህጋዊ የማንነት መረጃዎች ላይ በመመሥረት መፈፀም በሚያስችል አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ሥርዓት ካልተመሩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት አካል የሆነውን የግለሰቦችን የመምረጥና የመመረጥ መብት ማክበርም ሆነ ማስከበር አይቻልም። በመሠረቱ በህዝባዊ ምርጫ ስርዓት አፈፃፀም የመርሁ ዋነኛ መሠረት እያንዳንዱን መራጭ ማንነት ማለትም ህጋዊ ስም፣ ዜግነት እና የትውልዱን ቀንና የትውልድ ቦታውን የሚገልጽ መታወቂያ መኖር ነው። ለዚህ መታወቂያ ህጋዊነት ወሳኝ የሆኑት መረጃዎች የሚመነጩት ከግለሰቡ ህጋዊ የልደት መዝገብ ላይ ከተዘጋጀው የልደት ምስክር ወረቀት ነው። እዚህ ላይ የልደት መዝገብ ሲባል በመንግሥት ሰነድነት የሚታወቀው ሲሆን የልደት ምስክር ወረቀት ደግሞ ግለሰቡ ወዲያው እንደተወለደ በልደት መዝገቡ ላይ በመመሥረት የሚዘጋጅና ለግለሰቡ በወቅቱ የሚሰጠው ህጋዊ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ ግለሰቡ በአካባቢው አስተዳደር የነዋሪነት መታወቂያ በሚዘጋጅለት ወቅት በኗሪነት መታወቂያው ውስጥ ለሚገቡ መረጃዎች ህጋዊነት መነሻ ማስረጃዎች ምንጭ ነው። ስለሆነም ግለሰቡ የመመረጥ ወይም የመምረጥ መብቱ ተጠብቆለታል ሊባል የሚቻለው ከላይ በተገለፀው መሠረት በሀገሪቱ የምርጫ ህግ የሚካተቱ መሠረታዊ መመዘኛዎችን ማሟላቱን የሚያረጋግጡ ህጋዊ መረጃዎችን በማቅረብ የመብቱ ተጠቃሚ የሚያደርገው ህጋዊ የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት ሲኖር ብቻ ነው። እነዚህም ግለሰባዊ የማንነት መረጃዎች ህጋዊነታቸው የሚረጋገጠው በግለሰቡና በመንግሥት በጣምራ መያዛቸውን የሚያረጋግጥ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር ሲኖር ብቻ ነው።

2. እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን (ቀበሌ) ድረስ ለሕዝብ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ ግለሰባዊ የሕግ መረጃዎችንና ለፖሊሲና ፕሮግራም ዝግጅት፣ አፈጻጸምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ መሠረት የሆኑ ቀጣይና ወቅታቸውን የጠበቁ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን በማስገኘት፣

ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ሁለት ዋነኛ የመረጃ ውጤቶች ይገኛሉ። አንደኛው ግለሰባዊ የሕግ መረጃዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ናቸው። ግለሰባዊ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች

ለሶስት መሠረታዊ ጉዳዮች ግብዓት በመሆን ያገለግላሉ። እነርሱም ለሕግ አፈፃፀም ሥርዓት፣ ለአስተዳደርና ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ እና የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃን ለማጠናቀር ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ እስከዛሬ ለነዚህ ሶስት መሠረታዊ ግልጋሎቶች ግብዓት የሚሆኑ በአግባባዊ አሠራር የተዘጋጁ ግለሰባዊና ህጋዊ የስነ-ህዝብ መረጃዎች የሉም። ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም የሚታሰበው የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ ጥንቅር በግብአትነት ወይም አገልግሎት በመስጠት አስፈላጊ የሆኑትን ግለሰባዊና ህጋዊ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነት መረጃዎችን ለማስገኘት ያስችላል።

የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ በአንድ ሀገር በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት በማናቸውም የአስተዳደር ዕርከን ሊከናወኑ ለታሰቡ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድ ዝግጅቶች መነሻ መሠረት ነው። ይህም ሲሆን የተገኘው መረጃ ተገቢውን ግልጋሎት መስጠት እንዲችል ጥራቱ አስተማማኝ፣ ለዕቅድ አፈፃፀምና አተገባበር የሚያመች፣ ልማቱ ወይም አገልግሎቱ የሚመለከተውን ግለሰብ/ቤተሰብ ለመለየት በሚያስችል መልኩ መሰብሰብ/መዘጋጀት ይኖርበታል። ከዚህም በላይ የአፈፃፀም ሥርዓቱን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለመገምገም የሚያስችል ቀጣይና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለማስገኘት የሚችል ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የሚያደርሱ ለዕቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ ተፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የሚያስገኘውን የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃ ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት ማግኘት፣ ይህንንም የኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ከህዝብና ቤት ቆጠራና መሰል የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ከተገኙት መረጃዎች ጋር በማዛመድ መጠቀም ይገባል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ያለው የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት ሥርዓት በሀገር አቀፍ ከዚያም ሲወርድ በክልል መስተዳድሮች ለቆጠራው ዓመት ብቻ የሕዝብ ብዛትን በዕድሜ፣ በፆታና መሰል የስነ-ህዝብ መረጃዎች ከማስገኘት ባሻገር ከክልል መስተዳድሮች በታች ላሉ የአስተዳደር ዕርከኖች በቀጣይነትና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለመስጠት የሚያስችል አሠራር የለም። በየአሥር ዓመቱ የሚካሔደውና በሕዝብ

ቆጠራው የሚገኘው መረጃ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የህዝብ ብዛት መረጃን ለቆጠራው ዓመት የሚያስገኝ ቢሆንም በቆጠራዎች መሀከል ማለትም በ10ዓመቱ ውስጥ ላሉ ዓመታት አስተማማኝና ዘላቂ የሕዝብ ብዛት መረጃን ለማስገኘት ዓመታዊ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን ከምዝገባ ሥርዓቱ ማግኘትን ይጠይቃል። ከዚህም በተጨማሪ ከሕዝብ ቆጠራው የሚገኘውን የሕዝብ ብዛትና ባህርያት መረጃ በአስተማማኝ አሰራርና መረጃ ላይ በመመሥረት ወደ ቀጣይ ዓመታት ለመተንበይ እንዲሁ ዓመታዊ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ምጣኔዎች ያስፈልጋሉ። እስካሁን ድረስ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት በኢትዮጵያ ባለመዘርጋቱ በዚህ የምዝገባ ሥርአት መገኘት የሚገባቸው የሕዝብ ብዛት የምጣኔ መረጃዎች ስለሌሉ ትክክለኛውን የሕዝብ ብዛት እድገት ምጥነቱንም ሆነ የየዓመቱን የህዝብ ብዛት መረጃ እስከ ዝቅተኛው (ቀበሌ) የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት አልተቻለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ቀደም ሲልም ሆነ በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍም ሆነ በተዋረድ የሚዘጋጁ ዕቅዶች በአስተማማኝ የስነ-ህዝብ መረጃ ላይ እንዲመሠረቱ ለማድረግ ካለመቻሉም በላይ ዕቅዶቹን በየዓመቱ ለማደስም ሆነ የዕቅዶቹን አፈፃፀም እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለመከታተል የሚያስችሉ ቀጣይና ወቅቱን የጠበቀ የስነ-ህዝብ መረጃ ግብዓት ማዘጋጀት/ማቅረብ አልተቻለም። ምናልባት አንዳንድ ወገኖች የሕዝብና ቤት ቆጠራውን መረጃ መሠረት በማድረግ የተደረጉ የትንበያ መረጃዎችን በማየት ከላይ በተገለፀው መልክ የቀረበውን የመረጃ ክፍተት እያሚሉ ያሉ ሊመስላቸው ይችላል። በመሠረቱ ለሕዝብ ብዛት ትንበያ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑትና ከምዝገባ ሥርዓት መገኘት የሚገባቸው የልደትና የሞት ምጣኔዎች በሌሉበት ሁኔታ በጊዚያዊነት የተፈጠረ አሠራርን ተከትለው የተገኙ መረጃዎች ሀገሪቱ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የምትፈልገውን የስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎት ለማሙዋላት አይችሉም።

ስለሆነም የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት በሀገሪቱ መቋቋምና ማደግ መንግሥት ለሕብረተሰቡ ሊሰጣቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎቶችን አስቀድሞ ለማቀድ እንዲችል ከማድረጉም በላይ አገልግሎቱ ሊደርሰው ለሚገባ ግለሰብ በወቅቱ ለመስጠት የሚያስችል የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት ያስችለዋል። ለዚህም ቀጣይና /ቢያንስ በየዓመቱ/ ወቅቱን የጠበቀ በዋነኛነት የልደትና የሞት ምጣኔ

መረጃዎችን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን /ቀበሌ መስተዳድር/ ድረስ መረጃ የሚያስገኘውን የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃ ስርዓት መዘርጋት ግድ ነው።

## 2.1 ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙት ዋና ዋና የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃዎች

### 2.1.1 የየዓመቱን የልደት መጠን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የልደት መጠን መረጃ የሚገኘው በዋነኛነት በየ10 ዓመት ከሚካሄዱ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ነው። በሕዝብ ቆጠራ መረጃ ላይ በመመሥረት በስሌት በሚገኙ የትንበያ የልደት መጠን መረጃዎች ለሀገር አቀፍና ለክልል መስተዳድሮች የሚሆን የህዝብ ብዛት ትንበያ መረጃ ይዘጋጃል። ከክልል መስተዳድሮች በታች ላሉ የአስተዳደር ዕርከኖች ግን እንኳንስ በየዓመቱ ለቆጠራው ዓመትም ቢሆን አስተማማኝ የልደት መጠን መረጃ የለም። ስለሆነም ለየአስተዳድር ዕርከኑ ዓመታዊ የህዝብ ብዛት መረጃ መስጠት አልተቻለም።

### 2.1.2 የየዓመቱን የሞት መጠን/የህፃናትንና የአዋቂዎችን እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት/ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፡

እንደ ልደት ምጣኔ መረጃ ሁሉ የሞት ምጣኔ መረጃም በዋነኘነት በየ10 ዓመት ከሚካሄዱ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ይገኛል። የሞት ምጣኔ መረጃ የሕዝብ ብዛት መረጃዎችን ለማስላት ከሚያስገኘው ጥቅም በተጨማሪ የህዝቡን የጤና ደረጃ መለኪያ ዋነኛው መረጃ ነው። የሞት ምጣኔ መረጃ ከልደት ምጣኔ በተለየ ለአጠቃላዩ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በተለይ ለህፃናት፣ ለጎልማሶች፣ ዕድሜአቸው ለገፉ እንዲሁም ለእናቶች ተለይቶ መዘጋጀት ይገባዋል። በዚህ መልክ ተከፋፍሎ የሚዘጋጅ የሞት ምጥነት መረጃ የአንድን ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሒደት አልፎም የሀገሪቱን የጤና ደረጃ መገመቻ መለኪያ ተደርጎም ይወሰዳል። ስለሆነም የሞት ምጣኔ በተለይ የህፃናትና /ለተለያየ ዕድሜ/ የእናቶች የሞት ምጥነት መረጃ በቀጣይነትና /ቢያንስ በየዓመቱ/ ወቅቱን ጠብቆ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን /ቀበሌ መስተዳድር/ መገኘት

ይገባዋል። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ ወይም በክልል መስተዳድር ግምታዊ የሞት ምጥነት መረጃ በዋነኝነት በቆጠራ ወቅት ከመገኘት ባሻገር ከክልል መስተዳድር በታች ላሉ አስተዳደሮች መረጃው በየዓመቱ አይዘጋጅም።

### 2.1.3 ለሞት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች መረጃን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፣

በማናቸውም የዕድሜ ክልል ላሉ ሰዎች ተገቢውን የጤና ግልጋሎት ለመስጠት ከሞት ምጣኔ በተጨማሪ የሞት መንስኤ/ምክንያት መረጃዎች መገኘት አስፈላጊ ነው። በተከታታይ የሚሰበሰብና ወቅቱን ጠብቆ የሚቀርብ የሞት መንስኤ መረጃ በሌለበት ሁኔታ የጤና አገልግሎትም ሆነ የጤና አገልግሎት ዕቅድና ፕሮግራም በተገቢው መንገድ እየተከናወነ ነው ለማለት አይቻልም። እስከአሁን ድረስ አግባባዊውን የመረጃ አቅርቦት በተከተለ አሠራር የተዘጋጀ የሞት ምክንያት መረጃ በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል መስተዳድሮች ቀርቦ አያውቅም። የሞት ምክንያት መረጃ አቅርቦት አግባባዊው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት በሚጠናቀረው በወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ሥርዓት አማካይነት ነው። ስለሆነም በተለይም የወሳኝ ኩነት መረጃ ሥርዓትን በኢትዮጵያ ለማቋቋም ካለው ፍላጎት በዋነኛነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የሞት ምክንያት መረጃን በሁሉም የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት ነው። የሞት ምክንያት መረጃ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የስነ-ህዝብና ማህበራዊ ስታትስቲክስ መረጃ ፍላጎት በላይ የተለያዩ የጤና ጥናትና ምርምሮችን ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

### 2.1.4 የየዓመቱን የጋብቻ መጠን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፣

ምንም እንኳ ጋብቻ በሕዝብ ብዛት ምጥነት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖረውም በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአገልግሎት ፍላጎቶችን ለመለካት ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መረጃ ይሰጣል። ከዚህም በላይ የጋብቻ መረጃ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን በቀጣይነትና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ መገኘት ለበርካታ የስነ-ህዝብና ሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች ጥናትና ምርምር ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

### 2.1.5 የየዓመቱን የፍቺ መጠን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፡

ፍቺ እንደ ጋብቻ ሁሉ በሕዝብ ብዛት ምጥነት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖረውም በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአገልግሎት ፍላጎቶችን ለመለካት ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መረጃ ነው። ከዚህም በላይ እስከ ዝቅተኛው የአስተደዳደር እርከን በቀጣይነትና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ መገኘት ለበርካታ የስነ-ህዝብና ለሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች ጥናትና ምርምር ለማድረግ መረጃው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

### 2.1.6 የጋብቻ ዕድሜ ስርጭት መረጃን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ማስገኘት፡

የህዝብ ብዛት ዕድገትን ለመቆጣጠር የመጀመሪያ ጋብቻ ዕድሜ አንዱ የመረጃ ምንጭ ነው። የጋብቻ ዕድሜ አግባባዊው የመረጃ ምንጭ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት ነው። እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት ባለመኖሩ አስተማማኝ የጋብቻ ዕድሜ መረጃ ተዘጋጅቶ አያውቅም። በመሆኑም በመስኩ የተለያዩ የማህበረሰባዊ ፖሊሲ እርምጃዎችን እስከ ዝቅተኛው አስተዳደር ዕርከን በአስተማማኝ መረጃ ላይ በመመሥረት ተግባራዊ ለማድረግ የጋብቻ ዕድሜ መረጃ በቀጣይነትና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ የሚገኝበትን የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ማቋቋም የግድ ያስፈልጋል።

### 2.1.7 ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ በተፈጥሮ ክስተቶች (በልደትና ሞት) የሚጨምረውንና የሚቀንሰውን የህዝብ ቁጥር በየዓመቱ አልፎም ባነሰ ጊዜ ለማስላት የሚያስችል መረጃ ማስገኘት፤

በአንድ ድንበሩ በተከለለ አካባቢ የሚኖር ህዝብ የሕዝብ ቁጥርን የሚወስኑት መንስኤዎች የልደት፡ የሞትና የፍልሰት ኩነቶች ናቸው። በመጨረሻ ከተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ በመነሳት የአንድ አስተዳደር አካባቢ የህዝብ ብዛት መጠንን ለማስላት የአካባቢው ዓመታዊ የወሊድ እና የሞት መጠን መረጃዎች የግድ ያስፈልጋሉ። በዚህ ረገድ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ዓመታዊ የልደትና የሞት ምጥነትን የሚያስገኝ የመረጃ ሥርዓት በሀገሪቱ ባለመኖሩ በተለይም ከክልል በታች ላሉ የአስተዳደር ዕርከኖች ከመጨረሻ ቆጠራ በኋላ ወይም በቆጠራዎች

መሃከል የሕዝብ ብዛት መረጃ መስጠት አልተቻለም። ይኸ የሚያሳየው በየአስተዳደር ዕርከኑ የሚዘጋጁ የልማት ዕቅዶችም ሆኑ የአፈፃፀም ስልቶች ለማናቸውም የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ አሠራሮች መሠረት የሆነውን አስተማማኝ የሕዝብ ብዛት መረጃ ካልያዙ ከፍተኛ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከምትከተው ያልተማከለ የአስተዳደር አደረጃጀት አልፎም ወረዳን ማዕከል ያደረገ የዕቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም ግምገማ ስትራተጂ አንፃር የየወረዳውን ዓመታዊ የህዝብ ብዛትና ባህርያት የሚያሳይ መረጃ አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ለሀገሪቱ ዕድገት ወሳኝ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም።

## 2.2 በዝቅተኛ የአስተዳደር ዕርከን (በገጠር/በከተማ ቀበሌ) ልዩ ልዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎቶች ፈላጊ ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን ለይቶ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር መረጃዎችን በተቀናጀ አሰራር በወቅቱ ማቅረብ፣

በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ ለእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥና ክትትል፣ እንዲሁም የበሽታዎች ሥርጭትና ክትትል ሥርዓትን ለመፍጠር *(ለምሳሌ ለክትባት አሰጣጥ፣ የተላላፊ በሽታ መከሰት ጠቋሚ መረጃዎችን ለማግኘት፣...)*፣ የወሊድ መከላከያ አገልግሎት አሰጣጥና ክትትል፣ ልዩ እንክብካቤ የሚፈልጉ እናቶችና ህፃናት ጤና ክትትል *(ሲወለዱ ክብደታቸው ያነሱትን ህፃናት ጤና ለመከታተል፣ በወሊድ ጊዜ የተፈጠሩ ውስብስብ ችግሮች (Complications) ያሉባቸውን እናቶች ጤና ለመከታተል፣ ሲወለዱ ወይም ከወሊድ በኋላ የአካል ጉድለት ያለባቸውን ልጆች ጤና ለመከታተል፣ . . . )*፣ በኑሮአቸው ወይም በጤናቸው ምክንያት ልዩ እንክብካቤ የሚፈልጉ ቤተሰቦችን ለመለየትና ደህንነታቸውን ለመከታተል *(ብዙ ልጆች ያሉዋቸውና በኑሮአቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቤተሰቦችን፣ ወላጆቻቸው በህይወት የሌሉ ልጆችን ወይም በወላጆች መለያየት ምክንያት ክትትል የሚፈልጉ ልጆች ያሉባቸው ቤተሰቦችን ለመለየት፣ ...ወዘተ)* እና ለመሳሰሉ የዕለት ተዕለት የማህበራዊ አገልግሎትና የአስተዳደር ተግባር የሚፈለጉ መረጃዎችን ለማስገኘት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ የኩነት ምዝገባ ሥርዓትን መዘርጋት የግድ ያስፈልጋል። ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በትንሹ የአስተዳደር እርከን

ደረጃ (የቀበሌ አስተዳደር) ከሚጠናቀሩ ልደትንና ሞትን ከተመለከቱ መረጃዎች ጥቂቶቹ ከታች ቀርበዋል።

ሀ. <u>ለዕለታዊ መረጃ ፍላጎት</u> - ግለሰባዊ መረጃዎች በትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ

1. በቀበሌው ውስጥ የተወለዱ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
2. በቀበሌው ነዋሪ ከሆኑ ወላጆች የተወለዱ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
3. ሲወለዱ ከብደታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
4. ሲወለዱ ወይም ከተወለዱ በኋላ የአካል ጉድለት ያለባቸው ህፃናት በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
5. ሲወልዱ ወይም ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሞቱ እናቶች በዕድሜ እና በአድራሻ ዝርዝር
6. በወቅቱ የወለዱ እናቶች ከአሁኑ ልጅ በፊት የወለዱዋቸውና በህይወት ያሉ ልጆች ብዛት እና በአድራሻ ዝርዝር፣
7. የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ የወለዱ እናቶች በወሊድ ጊዜ በተደረገ ዕርዳታ ዓይነት/በወሊድ ቦታ /ሆስፒታል፣በቤት ውስጥ፣ በልምድ አዋላጅ፣.... / እና በአድራሻ ዝርዝር፣
8. የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ የወለዱ እናቶች በወሊድ ጊዜ ልጆቻቸው የሞቱባቸው በአድራሻ ዝርዝር፣
9. የቀበሌ ነዋሪ የሆኑና የወለዱ እናቶች አሁን የወለዱት ልጅ ከቀድሞው ልጅ ያለው የጊዜ ልዩነት በአድራሻ ዝርዝር፣
10. የቀበሌ ነዋሪ የሆኑና የመጀመሪያ ልጅ የወለዱ እናቶች በአድራሻ ዝርዝር፣
11. በቀበሌው ውስጥ በተላላፊ በሽታ የሞቱ በፆታ እና በአድራሻ ዝርዝር፣
12. በቀበሌው ውስጥ ዕድሜአቸው ከ0-4 ዓመት የሆኑ የሞቱ ልጆች በአድራሻ ዝርዝር፣

*አድራሻ ሲባል ግለሰቦችን በመኖሪያ ቤት የቤት ቁጥርና መሰል መረጃዎች ለይቶ ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ማለት ነው።*

ለ. <u>ለወርሃዊ መረጃ ፍላጎት-</u> ጥቅል መረጃዎች - ከትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ጀምሮ

1. በወሩ ውስጥ የተወለዱ ልጆች ብዛት በፆታ፣
2. በወሩ ውስጥ የወለዱ እናቶች ብዛት በዕድሜ፣
3. በወሩ ውስጥ የወለዱ እናቶች ብዛት በወለዱበት ቦታ የጤና ተቋም በቤት ውስጥ፣.../
4. በወሩ ውስጥ የወለዱ እናቶች ብዛት በመደበኛ መኖሪያ ቦታ፣
5. በወሩ ውስጥ የተወለዱ ልጆች በወላጆች የጋብቻ ሁኔታ፣
6. በወሩ ውስጥ የተወለዱ ልጆች በወላጆቻቸው በህይወት የመኖር ሁኔታ፣
7. በወሩ ውስጥ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በፆታ፣
8. በወሩ ውስጥ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በሞት ምክንያት፣
9. በወሩ ውስጥ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በተወለዱበት ቦታ፣
10. በወሩ ውስጥ የተወለዱ ልጆች ሲወለዱ በነበራቸው ክብደት እና በፆታ፣
11. በወሩ ውስጥ የተወለዱ ልጆች በልደት ዓይነት /አንድ፣መንታ፣ ሶስት፣/
12. በወሩ ውስጥ ሲወለዱ ወይም ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሞቱ እናቶች በዕድሜ፣

# አጠቃላይ መግለጫዎች

*(ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ጥቅል መግለጫዎች ቀደም ሲል በኮሚሽኑ ጽ/ቤት የቫይታል ስታትስቲክስ ምዝገባ ጥናትና ምርምር መምሪያ ከተዘጋጁ ልዩ ልዩ የግምገማ የቴክኒክ ጥናቶች ላይ በመመሥረት ተጠቃለው የቀረቡ ናቸው። እነዚህ በጽሁፉ በተለያየ ቦታ የተጠቀሱት የጥናት ዶኩመንቶች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመስኩ ካዘጋጃቸው የቴክኒክ መመሪያዎች እና በአህጉር አቀፍና የልዩ ልዩ ሀገሮች ተሞክሮዎች እንዲሁም በሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ቀደም ያሉ የጥናት ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ የተዘጋጁ ናቸው። ይኸ የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን በመዘርጋት ባለቤትና ተባባሪ ለሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ቀርቦ በውይይት እንደሚዳብር ይጠበቃል።)*

## II በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ምን ዓይነት ይሁን?[4]

### 1. በዓለም አቀፍ ደረጃ የምዝገባ ሥርዓት አወቃቀር መሠረተ-ሀሳቦች፤

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ መመሪያዎች በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አወቃቀር ሁለት መሠረታዊ አደረጃጀቶችን በግልጽ በመለየት መዋቀር እንደሚገባው ይገልፃል። እነርሱም የምዝገባ ሥርዓቱን "ድርጅታዊ" እና "አስተዳደራዊ" አወቃቀር ይመለከታሉ።

- በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ "ድርጅታዊ" አወቃቀር ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል። ይኸውም "የተማከለ" ወይም "ያልተማከለ" አደረጃጀት በመከተል ሊዋቀር ይችላል።
- በሌላም በኩል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ "አስተዳደራዊ" አወቃቀር የተለያየ መልክ ይዞ ሊደራጅ ቢችልም በዋነኝነት ተለይተው የሚታወቁት አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች፦
  * ራሱን ችሎ የሚተዳደር የምዝገባ ሥርዓት እና
  * ራሱን ችሎ የማይተዳደር (በሌላ ተቋም ሥር የሚተዳደር) የምዝገባ ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ።

ከዚህ አንፃር የአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር የሀገሪቱን ሥርዓተ-መንግስት አደረጃጀትና የመንግስት ተቋማትን አስተዳደራዊ አወቃቀር መሠረት ባደረገ ጥናት ላይ በመመሥረት ሊደራጅ ይገባል።

---

[4] በዚህ ጽሁፍ የቀረበውን አደረጃጀት የሚያሳየው መዋቅራዊ ቻርት በውይይት ወቅት ይቀርባል።

2. በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሊከተል የሚገባው "ድርጅታዊ" አወቃቀር ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል? ለምን?

በአንድ ሀገር የምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር የተማከለ ወይም ያልተማከለ መሆኑን ለመወሰን አስቀድሞ ሙያው በሚመለከተው/ታቸው ተቋም/ማት ጥልቅ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል። በዚህ መስክ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በተከታታይ ባደረጋቸው የግምገማ ጥናቶች መሠረት በዋንኛነት ሀገሪቱ ከምትከተለው የፌደራል ሥርዓት-መንግስት አስተዳደር አንፃር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱ ድርጅታዊ አወቃቀር "ያልተማከለ" ሊሆን እንደሚገባ በጥናቱ ውጤት ገልፆ ይገኛል። ይኸም ማለት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባርን የማከናወኑና የማስፈፀሙ ሥራና ኃላፊነት የክልል መስተዳድሮች መሆን እንደሚገባው ተመልክቷል። ይህም ሆኖ በየክልል መስተዳድሩ የሚከናወነውን የምዝገባ ሥራ የቴክኒክ ብቃት የሚከታተልና የሚገመግም እንዲሁም ተመሳሳይነት ያላቸው ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች የሚዘጋጁበትን አሠራር የሚያደራጅ ሀገር አቀፍ መንግስታዊ ተቋም እንደሚኖር ይታሰባል። እንደሚታወቀው በአንድ ሀገር የምዝገባ ሥራ ያልተማከለ በሚሆንበት ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን ሥራ የሚያስተባብርና ሀገራዊ ይዘቱን የሚከታተል ሀገራዊ የቴክኒክ ተቋም መኖሩ ግድ ነው። ከዚህም በላይ ይህ ተቋም የሀገሪቱን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ የሚያጠናቅርና የሚያሰራጭ እንዲሁም የሀገሪቱ የምዝገባ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት ሆኖ የሚያገለግል ቢሆን ይመረጣል።

3. በኢትዮጵያ የምዝገባ ሥርዓቱ ሊከተል የሚገባው "አስተዳደራዊ" አወቃቀር ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል? ለምን?

የአንድ አገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስተዳደራዊ አወቃቀር/አደረጃጀት ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚገባ ለመወሰን ዋነኛውና ወሳኙ ጉዳይ የሀገሪቱ ተጨባጭ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የዕድገት ደረጃና የሕዝብ አስተዳደር ተቋማዊ አወቃቀር ነው። ይኸም ሆኖ የኩነቶች ምዝገባ ተግባር መከናወን የሚገባው ለሕብረተሰቡ ቅርብ በሆነው በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን መሆን እንደሚገባው የምዝገባ ሥርዓቱ ዓለም አቀፍ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አሠራር መርህ ያዛል። እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የህዝብ

አስተዳደር መዋቅር አደረጃጀት መሠረት ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የቀበሌ መስተዳድር ነው። የቀበሌ መስተዳድር የዕዝ ሰንሰለትም እስከ ክልል መስተዳድር የሚደርስበት ሥርዓት ተዘርግቶ ይገኛል። በመሆኑም በኢትዮጵያ የምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊ አወቃቀርና አደረጃጀት ይኸንኑ የአስተዳደር ዕርከን ተከትሎ የሚዋቀር ሊሆን ይገባል። ከዚህ በታች በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ መስተዳድር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባር አፈፃፀም በአጭሩ ተገልጿል፡፡

## የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈፃፀም በዝቅተኛው (በቀበሌ) የአስተዳደር ዕርከን፤

በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር አወቃቀር የወሳኝ ኩነት ምዝገባውን በመፈፀም ከቀበሌ መስተዳድር የተሻላ ተቋም ሊኖር ይችላል የሚል ግምት የለም። በመሆኑም የኩነቶች አመዘጋገብ ሥርዓት በምዝገባ ህጉ በሚገለፀው መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት በቀበሌው መስተዳድር ጽ/ቤት ሥር ማደራጀት ይገባል። በተጨማሪም እንደ ቀበሌው ስፋትና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ንዑስ የምዝገባ ጣቢያዎች በቀበሌው ሥር ሊቋቋሙ ይችላሉ።

## የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈፃፀም በወረዳ መስተዳድር ዕርከን፤

በኢትዮጵያ በተዋቀረው ያልተማከለ የሕዝብ አስተዳደር አደረጃጀት መሠረት የወረዳ መስተዳድሮች ሚና ሰፊና ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል። ከአለም አቀፍ ተሞክሮም ሆነ በተባበሩት መንግስታት ግምገማ መገንዘብ እንደሚቻለው የኩነቶች ምዝገባ ተግባር የሚፈፀመው በዝቅተኛው የአስተደደር ዕርከን ማለትም በሀገራችን በቀበሌ መስተዳድር ሥር እንደሚሆን ይጠበቃል። ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶችን ዕውቅና የመስጠቱና ሀገር አቀፍ የህዝብ መለያ ቁጥር ለእያንዳንዱ ግለሰብ የመስጠቱ ተግባር በወረዳ መስተዳድር ሥር መሆን እንደሚገባው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ጥናት ያመለክታል። ስለሆነም የወረዳ መስተዳድሮች የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላሉ። የወረዳው የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹምም የወረዳው አስተዳዳሪ ይሆናሉ። ይኸንኑ መሠረት በማድረግ የወሳኝ ኩነት መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀምን መሠረት ያደረጉ ሁለት ኮሚቴዎች በወረዳ መስተዳድር ሥር ይቋቋማሉ።

እዚህ ላይ በወረዳው መስተዳድር ሥር የሚገኙና ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች በራሳቸው የክብር መዝገብ ሹም እንዲኖራቸው ተደርጎው ሊዋቀሩ ይችላሉ።

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም በክልል መስተዳድር ዕርከን፤

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባር ያልተማከለ አደረጃጀት እንደሚኖረው ተገልፆአል። ስለሆነም የክልሉን የምዝገባ ተግባር የማቀድ፣ የማስፈፀምና የመቆጣጠር ሥራ የክልል መስተዳድሩ ይሆናል። በክልሉ መስተዳድር ሥር ይኸንኑ ተግባር የሚያከናውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽ/ቤት ይቋቋማል። ጽ/ቤቱንም የሚመሩት ክልሉን በመወከል የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባል የሆኑት የክልሉ መስተዳድር ሥራ አስፈፃሚ አባል እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

4. በኢትዮጵያ የምዝገባ ሥርዓቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያስተባብረው የመንግስት ተቋም ማን ቢሆን ይመረጣል? ለምን?

ያልተማከለ ድርጅታዊ አወቃቀር የሚከተሉ የምዝገባ ሥርዓቶች በምንም መልኩ የወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊ መረጃ አመዘጋገባቸውና የሚያዘጋጁዋቸውም ህጋዊ የምስክር ወረቀቶች ተመሳሳይነት ያላቸው፣ ከሀገር አቀፍ አልፎ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሀገር አቀፍ ተቋም እንዲኖር ግድ ይላል። ይኸ ተቋም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን በሀገር አቀፍና በክልል የመስተዳድር ዕርከኖች እያጠናቀረ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ ቢሆን የየክልል የምዝገባ ተግባራትን የቴክኒክ የብቃት ደረጃ ለመገምገምና የምዝገባውን የሽፋን ደረጃ ለመለካት ያስችላል። በኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን ተግባር የማስተባበር ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚችል፣ በመረጃ ጥንቅርና ፍሰት አደረጃጀት የቴክኒክ ብቃት ያለው ተቋም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት እንደሆነ በጽ/ቤቱ በኩል በተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሁፍ ተንፀባርቆ ይገኛል። ለዚህም መነሻ የሆኑት ዋነኛ ምክንያቶች፦

4.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የሀገሪቱን የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚያጠናቅር በመሆኑ፣

4.2 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥራ በመሠረቱ የስነ-ሕዝብ መረጃ ማጠናቀር ሥራ አካል እንደመሆኑ በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በመስኩ ሰፊ ልምድ ያለው ሀገር አቀፍ ተቋም በመሆኑ፣

4.3 በየክልል መስተዳድሩ የሚካሄደውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥራ ለማስተባበር የሚያስችል አደረጃጀት በኮሚሽኑ መዋቅር የተካተተ በመሆኑ ነው።

## 5 በኢትዮጵያ የምዝገባ ሥርዓቱና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ማጠናቀሩ ተግባራት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አቀነጃጀት ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል?

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት ያልተማከለ እንደሚሆን ተመልክቷል። በአንፃሩ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችም ሆነ ከተባበሩት መንግስታት ምክር አንፃር በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት አደረጃጀት የተማከለ ሊሆን ይገባል። በመሠረቱ በዋነኝነት ለህግ አፈፃፀምና ለስታትስቲክስ መረጃ ጥንቅር የሚፈለገው የወሳኝ ኩነት የምዝገባ ተግባር በዝቅተኛ የአስተዳደር ዕርከን የሚከናወነው በአንድነት ወይም ጎን ለጎን በአንድ የወሳኝ ኩነት መዝጋቢ ነው። የወሳኝ ኩነት የምዝገባና የስታትስቲክስ መረጃ የአደረጃጀት ልዩነቱ የሚመጣው በኩነቶች መረጃ ማስተላለፍና አጠነቃቀር ላይ ይሆናል። ይኸውም ከምዝገባ ሥርዓቱ የተገኙትን ግለሰባዊ የኩነት መዝገቦች መሰረት በማድረግ (ወይም በስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾች አማካይነት የሚሰበሰበው) የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን እንዲያጠናቅር ለተቋቋመው ሀገር አቀፍ ተቋም በቀጥታ ሲላክ በአንፃሩ የምዝገባ መዝገቦች በየደረጃው ላሉ የምዝገባ ጽ/ቤቶች እንዲተላለፉ ይደረጋል።

## 6 በኢትዮጵያ የምዝገባውን ተግባር የሚያከናውነው የቀበሌ መስተዳድር የምዝገባ አፈፃፀም አደረጃጀት ምን ቢሆን ይመረጣል?

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ በገጠርም ሆነ በከተማ የቀበሌ መስተዳድሮች አወቃቀር ለሕብረተሰቡ ቅርብ ሆነው መቋቋማቸው የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓቱን ለመምራት እመቺ ቢያደርጋቸውም የመስተዳድሮቹ የውስጥ

አወቃቀርና የሰው ኃይል ጥንቅራቸው ለመረጃ ዝግጅትና የልማት ዕቅድ ሥራን በአግባቡና በብቃት ለመወጣት በቂ አቅም የላቸውም። በተለይም የህግና የስታትስቲክስ መረጃ ፍላጎትን ያሟሉ የወሳኝ ኩነት መረጃ የማደራጀት ተግባርን ለመወጣት የቀበሌ መስተዳድሮች ሰፊ የሰው ኃይል የአቅም ግምባታና መዋቅራዊ ብቃታቸውን ማሳደግ ይጠይቃል። በዚሁ መሠረተ ሃሣብ ላይ በመቆም የቀበሌ መስተዳድሮች በመዋቅራቸው ውስጥ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል የሥራ ዘርፍ ተለይቶ እንዲኖራቸውና የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ የኩነት መዝገቦች ተጠብቀው የሚቀመጡበት የመዝገብ ቤት አደረጃጀት ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ፣ ለነዚህም ተግባራት ቢያንስ አንድ ሠራተኛ ሊመደብ እንደሚገባ በቀረበው ጥናት ተመልክቷል። ለዚህም አሁን ያለው የገጠርና የከተማ ቀበሌ መስተዳድሮች ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል አቅርቦትና የመስተዳድሩ የሥራ መጠን በሥራ ክፍሎች ተለይቶ ዝርዝር ጥናት እንደሚደረግበት ይጠበቃል።

## 7 በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም በየትኛው የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ ላይ ቢሆን ይመረጣል? ለምን?

በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በቀረበው ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ቻርት መሠረት የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም በወረዳ አስተዳደር ዕርከን ደረጃ ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል። በዚህ መሰረት የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ ዋና ክፍሎች የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባርን በመፈፀም የኩነቶች መዝገብና የምስክር ወረቀት ቅጅዎችን ወደ ወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ይልካሉ። የወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ልዩ ልዩ የማጣሪያ ቴክኒካዊ አሠራሮችን በመከተልና መጠነኛ የኩነቶች የማጠናቀር ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡ የወረዳውን የወሳኝ ኩነት የምዝገባ ተግባር ክትትል ያደርጋሉ፡፡ በተለይም የምዝገባ ሥርዓቱን አሰራር ለመቆጣጠር እንዲረዳም ጭምር የተዘጋጀውን የህዝብ መለያ ቁጥር በመስጠትና የኩነቶችን ክስተት በመከታተል ህጋዊውን የኩነቶች ሰነድ ያፀድቃሉ። ይኸንኑ ትልቅ ሀላፊነት በመወጣት በኩል በአመዛኙ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ የወረዳ መስተዳድሮች በአሁኑ ወቅት ተገቢው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ያላቸው እንደሆነ የተገመተ ከመሆኑም በላይ በቀጣይነትም ወረዳዎች የአስተዳደርና የልማት

ማዕከል ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ይደረግላቸዋል የሚል ዕምነት አለ። በመሆኑም የወረዳ መስተዳድሮች የህዝብ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት በመሆን እንደሚያገለግሉና የወረዳ ርዕሰ-መስተዳድሮችም የህዝብ የክብር መዝገብ ሹሞች በመሆን እንደሚያገለግሉ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ጥናት ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ በወረዳ መስተዳድር ሥር የሚገኙ ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች የራሳቸው የክብር መዝገብ ሹም እንዲኖራቸው ሊደረግ ይችላል።

## 8 በኢትዮጵያ የምዝገባ ዋና ዳይሬክተር ማን ይሁን? ለምን?

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር ያልተማከለ እንደሚሆን፡ በአንፃሩ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር ደግሞ የተማከለ እንደሚሆን ተገልፆአል። ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባር አለም አቀፍ ተሞክሮ አኳያ ያልተማከለ ድርጅታዊ አወቃቀርን የሚከተሉ የምዝገባ ተግባራት ሀገራዊ አልፎም ዓለም አቀፋዊ መስፈርትን ያሟሉ የኩነት መረጃዎችን ለማስገኘት የኩነቶች መረጃን ቅርጽና ይዘታቸውን የሚቆጣጠርና የምዝገባውን አፈፃፀም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያስተባብርና የሚገመግም ተቋም እንደሚያስፈልግ ተመልክቷል። ከዚህ አንፃር ይኽንን በአመዛኙ ቴክኒካዊ ሥራና ኃላፊነት በብቃት ሊያከናውን የሚችለው ከምዝገባው ተግባር ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው (የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃን በማጠናቀርና በማሰራጨት) የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሊሆን እንደሚገባ በቀረበው ጥናት ተገልፆአል። በመሆኑም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ዋና ፀኃፊ የምዝገባ ዋና ዳይሬክተር በመሆን እንዲያገለግሉ ማድረጉ ከሁሉም የተሻለ አማራጭ ነው የሚል ዕምነት አለ።

## III በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል ምን ዝግጅት ተደርጓል?[5]

### 1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት መቼ ተቋቋመ? ዓላማውና ተጠሪነቱስ?

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 103 መሠረት ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሆነ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 180 /1991 ተቋቁሟል። የኮሚሽኑ አባላት ስብጥር ከዘጠኙ ክልሎች፣ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከፌዴሬሽን ምክር ቤትና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት የተውጣጡ እንዲሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 6 ተወስኗል። የኮሚሽኑ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ እንደሚሾሙም በአዋጁ አንቀጽ 5/1/ ተደንግጓል። የኮሚሽኑ አባላት ሹመትም ጥቅምት 6 ቀን 1995 ዓ.ም. ለሕዝብ ይፋ ሆኖአል።

ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት ሁለት መሰረታዊ ዓላማዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የኮሚሽኑ ዓላማ በመላ ሀገሪቱ በየ10 አመቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድን ሲመለከት ሁለተኛው ደግሞ በመላ ሀገሪቱ የሕዝብና ቤቶች ምዝገባ የሚቋቋምበትንና የሚሠራበትን መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ ነው። ይኸንኑ ሁለተኛውን የኮሚሽኑን ዓላማ መሠረት በማድረግ በሀገሪቱ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ማለትም የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋምና ለማሳደግ የሚያስችሉ መሠረታዊ ጥናቶችን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እያደረገ ይገኛል።

[5] በዚህ ጽሁፍ የቀረበውን አደረጃጀት የሚያሳየው መዋቅራዊ ቻርት በውይይት ወቅት ይቀርባል።

2. የኮሚሽን ጽ/ቤቱ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓትን በማቋቋም ሀላፊነቶችን ለመውሰድ የሚያስችሉት ምክንያቶች ምንድናቸው?

በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደተጠቀሰው በሀገሪቱ የህዝብ ማለትም የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት የሚቋቋምበትን መሠረታዊ ጥናቶች ጽ/ቤቱ እንዲያካሂድ ሃላፊነት ተጥሎበታል። በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ከምዝገባ ሥርዓቱ የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና በየአስተዳደር ዕርከኑ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለመረጃ ተጠቃሚዎች የማቅረብ ኃላፊነት በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር ተካቶ ይገኛል። የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ከምዝገባ ሥርዓቱ በቀጣይነትና በቋሚነት ለማስገኘት በሀገሪቱ የምዝገባ ሥርአቱ አስቀድሞ መቋቋም ይገባዋል። በመሆኑም የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማጠናቀር የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የምዝገባ ሥርዓቱ በሀገሪቱ እንዲቋቋም አስፈላጊ የቴክኒክ፣ የህግና የአስተዳደር ዝግጅቶች ላይ መሳተፍና ኃላፊነቶችንም በግንባር ቀደምትነት መቀበል ይጠበቅበታል።

3. የኮሚሽን ጽ/ቤቱ የምዝገባ ሥርዓቱን በማስፈጸም የሚኖረው ድርሻ ምን ይሆናል?

የኮሚሽን ጽ/ቤቱ በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓትን በማቋቋምና ሥርዓቱን በቀጣይነትና በቋሚነት በማካሄድ ሰፊ የተሳትፎ ድርሻ አለው። በመሆኑም በቅድሚያ የምዝገባ ሥርዓቱን በማቋቋም በኩል ከሀገሪቱ የህግና የአስተዳደር ሥርዓት ጋር የተጣጣመ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ቴክኒካዊ ጥናትን በማድረግ ሰፊ ድርሻ ይኖረዋል። ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓቱ ጋር በመቀናጀት የሚካሄደውን የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ሥርዓት በመዘርጋትም እንዲሁ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀሩን እንዲሁም የመረጃ ፍሰትና ከኩነቶች ምዝገባ ጋር ያለውን ቁርኝነት የሚያሳይ ጥናት ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህም ሂደት በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት የምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቱን ለመዘርጋት በሚወስነው

ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ጥናት ላይ በመመሥረት የሚሰጠውን የሥራ ድርሻ ይወጣል። በዚህ ረገድ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በኩል በተደረገው በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር ጥናት ውጤት መሠረት ጽ/ቤቱ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት እንደሚያከናውን ይጠበቃል።

3.1 በሀገር አቀፍ ደረጃ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓቱን አፈጻጸም ያስተባብራል፣ የቴክኒክ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ቴክኒካዊ አሠራሩን ይመራል፣ የመዝገቦችንና የምስክር ወረቀቶችን ቅርጽና ይዘት ተመሳሳይነት ይቆጣጠራል፤

3.2 የሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ዳይሬክተር መ/ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

3.3 የሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት በመሆን ያገለግላል፤

3.4 የሀገሪቱን የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃ ይሰበስባል፣ መረጃዎችን ይተነትናል፣ ጥናታዊ ሪፖርቶችንም በማዘጋጀት ውጤቱን ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

3.5 በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ መረጃን የሽፋንና የጥራት ግምገማዎችን ያደርጋል፣ አስፈላጊ የማስተካከያ የቴክኒክ መመሪያዎችን በማውጣት ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ያደርጋል፤

3.6 በሀገሪቱ የምዝገባ ሥርዓቱን አፈፃፀም የቴክኒክ ብቃት በማሳደግ በኩል የሰው ኃይል ስልጠና በቀጣይነትና በቋሚነት ያደርጋል፤

3.7 በሀገር አቀፍ ደረጃ ስለምዝገባ ሥርዓቱ አስፈላጊነት፣ የምዝገባ ሥርዓቱ ውጤት የሆኑ ግለሰባዊና የስታትስቲክስ መረጃዎች ጥቅም ላይ የተመሠረተ ቀጣይና ቋሚ ትምህርትና ቅስቀሳዎችን ያደርጋል፤ ህብረተሰቡም ህጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ እንዲመዘገብ በማድረግ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ቅስቀሳ ያደርጋል፤ የቅስቀሳ ማቴሪያሎች እያዘጋጀ ያሰራጫል፤

3.፰ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለመመሥረትና ለማሳደግ የተዘጋጀውን ብሄራዊ የድርጊት መርሀ-ግብር በመተግበር የሚሰጠውን ሀላፊነት ይወጣል።

4. የኮሚሽን ጽ/ቤቱ የሚጣልበትን ኃላፊነት ለመወጣት አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀሩ ምን ያህል አመቺ ነው?

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የፌዴራል መሥሪያ ቤት ሆኖ የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው። የኮሚሽን ጽ/ቤቱን የሚያስተዳድረው የሕ.ቤ.ቆ. ኮሚሽን የአባላት ስብጥር የዘጠኙን ክልሎች ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ አካላትን በአባልነት የያዘ በመሆኑ በሀገሪቱ የምዝገባ ሥርዓቱን አፈፃፀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር አመቺ ያደርገዋል። የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የሀገሪቱን የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃ በማጠናቀር የተሰጠውን ሀገራዊ ሃላፊነት ለመወጣት ያደራጀው የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ የሥራ ዘርፍ በሀገሪቱ የምዝገባ ሥርዓቱን አፈፃፀም ለማስተባበርና ቴክኒካዊ አሠራሩን ለመምራት የሚያስችለውን አደረጃጀት ጽ/ቤቱ እንዲይዝ ያደርገዋል። ከዚህም በላይ ኮሚሽኑ በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ከማናቸውም መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆነ ተቋም ጋር በትብበር ለመስራትና እንደየአስፈላጊነቱ ንብረትና የሰው ኃይል ለመጠቀም የሚችል በመሆኑ የምዝገባ ስራውን በክልልም ሆነ በማዕከል በማስተባበር የማስፈፀም ችግር አይገጥመውም፡፡ በተለይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት የኮሚሽኑ አባል መሆኑ በክልል መስተዳድሮች የባለሥልጣኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና የሰው ኃይል በትብብር በመጠቀም በኩል ሰፊ ዕድል ይሰጠዋል። በመሆኑም የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የምዝገባውን ተግባር በክልል መስተዳድሮች በማስተባበርና ቴክኒካዊ አሠራሩን በበላይነት በመምራት ድርጅታዊ አወቃቀሩ እንዲሁም ቴክኒካዊ አደራጃጀቱ ከማንም የፌዴራል መሥሪያ ቤት ተመራጭ ያደርገዋል።

5. የኮሚሽን ጽ/ቤቱ የምዝገባ ሥርዓቱን በማቋቋምና በማሳደግ የሚጣልበትን ሀላፊነት ለመውጣት ምን ዓይነት የአቅም ግንባታና የአደራጃጀት ለውጥ ሊያደርግ ይገባል?

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት በአምስት መምሪያዎችና አምስት አገልግሎቶች የተደራጀና በዋና ፀሐፊና በምክትል ዋና ፀሐፊ የሚመራ የፌዴራል መ/ቤት ነው። የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ በአሁኑ ወቅት በአንድ መምሪያ ደረጃ የተደራጀ ሲሆን በሥሩም ሁለት ኤክስፐርት ቡድኖች አሉት። ሁለቱ የኤክስፐርት ቡድኖች 16 የኤክስፐርት የሥራ መደቦች አሏቸው። መምሪያው ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት የተሰጠውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን በሀገሪቱ ለማደራጀት የሚያስችለውን መሠረታዊ ጥናት በማድረግ በኩል በአሁኑ ወቅት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በኩል ተዘጋጅቶ በቀረበው ጥናት መሠረት የሕ.ቤ.ቆ.ኮ. ጽ/ቤቱ በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት አፈፃፀምን የሚያስተባብርና የቴክኒክ ሥራውን የሚቆጣጠር ተቋም እንዲሆን ከተደረገ መጠነኛ የአወቃቀርና የአደረጃጀት ለውጥ ማድረግን ይጠይቃል።

6. የኮሚሽን ጽ/ቤቱ የምዝገባ ስርዓቱን በሀገሪቱ ለማቋቋም በሚደረጉ የዝግጅት እንቅስቃሴዎች ያከናወናቸው ዋና ዋና የዝግጅት ተግባራት፣

እንደሚታወቀው ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ማቋቋም መነሻ የአወቃቀር መሠረቱ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ነው። በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ዋነኛ ተግባር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ማከናወን፣ ሀዝብ-ነክ ናሙና ጥናቶችንና የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃዎችን በተለያዩ የአጠናን ዘዴዎች አማካኝነት ማካሄድ ነበር። እነዚህ የሥራ ዘርፎች ስፋትና ጥልቀት ተደርጎባቸው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋነኛ የአደረጃጀቱ መነሻና የተግባሩ መሠረት ሆነው እንዲቆዩ ተደርጓል። በዚህ ረገድ በተለይም የቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ቀደም ሲል በባለሥልጣኑ መ/ቤት በጥራታቸው የተሻሉ የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃዎችን የሚያስገኙ የአጠናን ዜዎችን በማካሄድ ላይ ተገድቦ የነበረውን አሠራር በመቀየር በሀገሪቱ የህግ፣ የአስተዳደርና የስታትስቲክስ መረጃዎችን በጣምራ የሚያስገኘውንና የቫይታል ስታትስቲክስ አግባባዊ የመረጃ ምንጭ የሆነውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የሚቋቋምበትንና የሚያድግበትን ቴክኒካዊ የአሠራር መሠረት የመጣል የዝግጅት ሥራውን ሲያከናውን ቆይቷል። ይህም ተግባር በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 4/2 በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ይህንኑም መሠረት በማድረግ ጽ/ቤቱ የሚከተሉትን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የዝግጅት ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

6.1 በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ሲቋቋም በቅደም ተከተል መከናወን ያለባቸውን ቴክኒካዊ ተግባራትንና በሚዘጋጀው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ መካተት ያለባቸውን ሃሳቦች የዓለም አቀፍ መርህን ከሀገሪቱ ተጨባጭ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዲሁም የአስተዳደር አደረጃጀት ጋር በማገናዘብ የሚያስረዳ ረቂቅ የቴክኒክ መመሪያ በቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ረቂቁ

ተዘጋጅቷል። ይኽ መመሪያ በሀገሪቱ በሚደረገው የምዝገባ ሥርዓት ማቋቋም ሀጋዊ፡ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ እንዲሁም የኩነቶች ምዝገባ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀርን በማስመልከት ለሚደረጉ የዝግጅት ተግባራት የቴክኒክ መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው።

6.2 ቀደም ሲል በተጠቀሰው የቴክኒክ መመሪያ (6.1) የተመለከተውን የወሳኝ ኩነቶች የአስተዳደርና ድርጅታዊ አወቃቀር መሰረት በማድረግ እንዲሁም በምዝገባ ህግ መሰረት ሀሳቦች ላይ በመመሥረት በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራ መመሪያ የሚሆነው የወሳኝ ኩነቶች የመዝጋቢዎች ረቂቅ በቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ተዘጋጅቷል።

6.3 የወሳኝ ኩነት መረጃዎች የሚመዘገቡት በመዝገብ ወይም በነጠላ ቅጠሎች ሊሆን ይችላል። ይኽንን አስመልክቶ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ፍሰትን መሠረት ያደረገ ጥናት ተደርጎ የቀረበ ሃሣብ አለ። ይኽንኑ መሠረት ያደረገ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቅርጽና ይዘት የሚያሳይ ቅጽ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም ቅርጽና ይዘታቸውን በሚገልጽ አኳኋን ለአራቱም ወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በተመሳሳይ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃዎች በምን ዓይነት አሠራር ይመዝገቡ የሚለው በጥናቶቹ ተካቶ በታየው መሠረት ሁለት አማራጭ አሠራሮች ላይ መሠረት ያደረገ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ ረቂቅ በቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ተዘጋጅቷል።

6.4 በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት እንዴት ይቋቋም የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ማቋቋም ዕቅድና የአፈፃፀም ስልትን የሚያሳይ ረቂቅ ዶክመንት በቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ተዘጋጅቷል።

6.5 ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱ የሚጠናቀረውን ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ በኮምፒውተር ለማስገባት፡ መረጃውን በስታትስቲካዊ ሠንጠረዦች ለማዘጋጀትና የትንተና ሪፖርቶችን ለማድረግ የሚያስችል የኮምፒውተር ፕሮግራም

የሚዘጋጅበት መንገድ በመጠናት ላይ ሲሆን አነስተኛ ሙከራዎችም በመደረግ ላይ ናቸው፡፡

6.6 ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትምህርትና ቅስቀሳ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጽሁፎች ተዘጋጅተዋል። ይኸውም በምዝገባ የሚገኝ የወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊና ጥቅል መረጃዎች ለግለሰቦች፣ ለማህበረሰብና ለመንግስት ስለሚያስገኙት ጥቅምና አስፈላጊነታቸው፣ በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር ምንነት፣ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች ይዘትና በተለይም ለግለሰቦች መረጃዎች በምን ዓይነት አስተዳደራዊ ሥርዓት ላይ በመመሥረት እንደሚሰጡ፣ ከእያንዳንዱ ግለሰብና የማህበረሰብ ክፍል ወሳኝ ኩነቶች ሲከሰቱ የትና በምን ያህል ጊዜ ማስመዝገብ እንደሚገባቸው እና የመሳሰሉ ዝርዝር ጉዳዩችን የሚገልፁ ጽሁፎች ተዘጋጅተዋል፣ በተጨማሪም በብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች የሚቀርቡ የትምህርትና ቅስቀሳ ጽሁፎች በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ።

6.7 በሀገሪቱ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባና ስታትስቲክስ አመሰራረትና እድገት የሚመለከት ሀገር-አቀፍ የድርጊት መርሀ-ግብር ተዘጋጅቷል። ይህ የድርጊት መርሀ-ግብር በክልል መስተዳድሮች ስምምነት ከተደረገበት በኋላ የሀገሪቱ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባና ስታትስቲክስ የፖሊሲ መመሪያ ዶኩመንት ሆኖ እንደሚያገለግል ይጠበቃል። የድርጊት መርሀ ግብሩ በቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ደረጃ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀ ሲሆን ወደፊት ለውይይት ለማቅረብ እንዲመች በአማርኛ ተተርጉሞ ይዘጋጃል።

## IV በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ግለሰባዊ መረጃዎችና የስታትቲስክስ መረጃ ፍሰት አደረጃጀት ምን ዓይነት ይሁን?[6]

### 1. በኢትዮጵያ ቅድሚያ የተሰጣቸው ወሳኝ ኩነቶች እነማን ናቸው?

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህዝብ የክብር መዝገብ አሠራርን አስመልክቶ በወጡ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጽሁፎች እንደተገለፀው ወሳኝ ኩነት ተብለው የሚታወቁት ልደት (Birth)፣ የሽል ሞት (Foetal death)፣ ሞት (Death)፣ ጋብቻ (Marriage)፣ ፍቺ (Divorce)፣ የጋብቻ መከናወንን መሰረዝ (ጋብቻ እንዳልተከናወነ መቁጠር) (Annulment of Marriages)፣ ባልና ሚስትን ለጊዜው በህግ መለያየት (Separation)፣ ጉዲፈቻ (Adoption)፣ በህጋዊ ጋብቻ ውስጥ ያልተወለደ ልጅን አባትነት ወይም እናትነት መቀበል (Recognition) ናቸው። ሆኖም በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም ቅድሚያ የተሰጣቸው ኩነቶች ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው።

### 2. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት መረጃ ፍሰት - አጠቃላይ

የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ፍሰት አደረጃጀት በመረጃዎች አሰባሰብ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር ላይ የተመሰረተ ነው። በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ቀደም ሲል በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በቀረበው የጥናት ሪፖርት ላይ ተመልክቷል። ይኸውም በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ድርጅታዊ አወቃቀር ያልተማከለ በመሆኑ የወሳኝ ኩነት ምዝገባው አፈጻፀም በክልል መስተዳድራት እንደሚተዳደር ተገልጾአል። ሆኖም ስለእያንዳንዱ የሀገሪቱ ዜጋ መወለድና መሞት እንዲሁም የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች መከሰት የሚገልጽ መረጃ ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነት መዝገብ ቤት በማደራጀት መከማቸት እንደሚገባው ተመልክቷል። በሌላም በኩል በክልል

---

[6] በዚህ ጽሁፍ የቀረበውን የመረጃ ፍሰት ሥርዓት የሚያሳየው ቻርት በውውይት መቅት ይቀርባል።

መስተዳድሮች ደረጃ የምዝገባው ተግባር መነሻ በሆነው የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዋና ክፍል የኩነት መዝገብ ቅጂ መኖር እንደሚገባው ተመልክቷል። በተጨማሪም የኩነቶች የክብር መዝገብ ቅጅዎችና የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ማለትም በወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች በሚዘጋጀው መዝገብ ቤት መቀመጥ እንደሚገባቸው ተገልጿል። ያልተማከለ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓትን በሚዘረጉ አሰራሮች የምዝገባ ቅጂዎችን በየክልል የምዝገባ አስፈፃሚ ተቋማት ማስቀመጥ ግድ ይሆናል። በዚህም ምክንያት በክልል መስተዳድሮች የሕዝብ የክብር መዝገብ መዝገብ ቤቶች መደራጀት ይኖርባቸዋል።

የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለማጠናቀር የሚያስፈልገው የምዝገባ መረጃ በተለያየ አኳኋን ሊሰበሰብ ይችላል። በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ አደራጃጀት ላይ በተደረገው ጥናት መሠረት ለህግና ለስታትስቲክስ የሚያገለግለው የምዝገባ መረጃ በአንድነት በአንድ መዝገብ መሰብሰቡ ተመራጭነት እንዳለው ተመልክቷል። በመሆኑም የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃን ማጠናቀር እንዲቻል ጭምር የመዝገብ ቅጅዎች ወደ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት እንዲላኩ ይደረጋል።

## 3. የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች ቅጂ ለባለመብቶች የመስጠቱና የአቀማመጥ ሥርዓቱ ምን ሊሆን ይገባል?

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት አንዱ ውጤት የኩነቱን መከሰትና ተዛማጅ ግለሰባዊ መረጃዎች ለግለሰቡ በምስክር ወረቀት መልክ አዘጋጅቶ መስጠት ነው። የኩነቶች ምስክር ወረቀት ለግለሰቦች የዕለት ተዕለት በርካታ የህግ ጉዳዮችና በአስተዳደር ግልጋሎት አሰጣጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ከዚህም በላይ በርካታ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስጠበቅ የግለሰቦች ህጋዊነት መረጃዎች መሠረት ናቸው። በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዐት አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀርን በሚያመለክተው የጥናት ውጤት ላይ እንደተመለከተው የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች ህጋዊነት የሚጸድቀው በወረዳ ደረጃ በሚሾመው የክብር መዝገብ ሹሙ ነው። በዚሁ መሠረት በቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል የተዘጋጁ የኩነት የምስክር ወረቀቶች ቅጂ እንዲፀድቁና የህዝብ መለያ ቁጥር

እንዲሰጣቸው ለወረዳው የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ይላካሉ። የወረዳው የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም የፈረሙባቸው የኩነት ምስክር ወረቀት ቅጂዎች ተመልሰው ወደ ቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል ይላካሉ። በቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል የሚገኘው መዝጋቢ አንዱን ቅጂ ለባለመብቱ፡ ሁለተኛውን ቅጂ ደግሞ በዋና ክፍሉ መዝገብ ቤት እንዲቀመጥ ያደርጋል።

## 4. ሀገር አቀፍ የሕዝብ መለያ ቁጥር የመስጠት ጥቅምና የአሰጣጥ ሥርዓቱ ምን ይመስላል? በማንስ ቢሰጥ ይመረጣል?

ሀገር አቀፍ የህዝብ መለያ ቁጥር ለእያንዳንዱ ልደት መስጠት ለበርካታ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራት ጠቀሜታ አለው። በተጨማሪም የምዝገባ ሥርዓቱን አፈፃፀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር ወሳኝ ድርሻ አለው። እንደሚታወቀው ልደት በአንድ ሰው ላይ የሚከሰተው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የልደት ምስክር ወረቀትም ለአንድ ሰው የሚዘጋጅለት በተወለደ በጥቂት ቀናት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ይኸም በመሆኑ ግለሰቡ በመወለድ ምክንያት የማህበረሰቡ አባል ሲሆን የአባልነት መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይገባል። ይህ የአባልነት መለያ ቁጥር በየዕድሜ ዕርከኑ ለሚፈልጋቸው ልዩ ልዩ ግልጋሎቶች መለያው ይሆናል። በተጨማሪም በየአስተዳደር ዕርከኑ የሚደራጁ የመረጃ ክምችቶችን በሥርዓት ለማስቀመጥና በተፈለጉ ጊዜም በቀላሉ ለማቅረብ እንዲቻል የህዝብ መለያ ቁጥሩ እንደ ቁልፍ መለያ በመሆን ያገለግላል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያየ አጋጣሚ ከአንድ ጊዜ በላይ የልደት ምስክር ወረቀት እንዲዘጋጅላቸው የሚጠይቁ ሰዎችን ለመቆጣጠር ያስችላል። የሕዝብ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ሀገራዊ ይዘትን ተከትሎ ለመስጠት በሚያስችል አሠራር መከናወን ይገባዋል። ስለሆነም የህዝብ መለያ ቁጥር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በምዝገባ ዋና ዳይሬክተር በሚወጣው ሀገር አቀፍ የሕዝብ መለያ ቁጥር አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ይፈጸማል። ይኸም ሲሆን የወረዳ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤቶች ለእያንዳንዱ ልደት የሕዝብ መለያ ቁጥር በመስጠት ይኸንኑ መለያ ቁጥር ለሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስተባባሪ ጽ/ቤት እንዲመዘግበው ያደርጋሉ።

5. በቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል የግለሰብ የኩነቶች መረጃ አቀማመጥና አደረጃጀት ምን ዓይነት ቢሆን ይመረጣል?

በኢትዮጵያ ቅድሚያ የተሰጣቸው ወሳኝ ኩነቶች አራት ሲሆኑ እነርሱም ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው። ለአራቱ ወሳኝ ኩነቶች የየራሳቸው መዝገብና የመረጃ ክምችት ይዘጋጅላቸዋል። ከዚህም በላይ የኩነቶች ቅጂ ምስክር ወረቀቶች በቀበሌው ምዝገባ ዋና ክፍል መቀመጥ የሚገባው ስለሆነ ለእያንዳንዳቸው ኩነቶች የተለየ ማከማቻ ይዘጋጃል። በቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል ውስጥ የኩነቶች ምዝገባውን ሥራ በኃላፊነት የሚያከናውን/ኑ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መዝጋቢ/ዎች ይመደባል/ሉ፡፡ በቀበሌ የሚመደብ መዝጋቢ/ዎች ከቀበሌው ቋሚ ቅጥር ሠራተኞች ወይም ለምዝገባው ሥራ ተብሎ የሚቀጠር በተለይም በህግ አፈፃፀምና በመረጃ አሰባሰብ ልዩ ስልጠና የተሰጠው ግለሰብ ይሆናል።

የቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል ለወሳኝ ኩነት ምዝገባ በሚዘጋጀው የአሠራር ሥርዓት መሠረት በቀበሌ ደረጃ የሚካሄዱ ተጓዳኝ የምዝገባ ተግባራትን የሚፈጽም ስለሚሆን ከነዚህ ተጓዳኝ ምዝገባዎች የተገኙ መረጃዎች ሲፈለጉ በቀላሉ ለማቅረብ በሚያስችል አኳኋን የሚቀመጡበት ቦታ እንዲዘጋጅላቸው ያስፈልጋል። ለአካባቢ ልማትና አስተዳደር አገልግሎት የሚፈለጉ የኩነቶች ዝርዝርን በማዘጋጀት ለቀበሌ አስተዳደርና የአካባቢ ግልጋሎት ለሚሰጡ ተቋማት መረጃዎችን እያደራጁ ማስቀመጥ የመዝጋቢው ተጓዳኝ የምዝገባ ተግባራት ናቸው። ስለሆነም መዝጋቢው በተለይ ለጤናና ትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግለሰባዊ የኩነት መከሰት መረጃዎችን በማጠናቀርና በማደራጀት በጥንቃቄ መረጃዎችን ይይዛል።

6. በሥራ ባህርያቸው ምክንያት ከወሳኝ ኩነቶች መከሰት ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት የኩነቶችን መከሰት በመጠቆም ድርሻቸው ምን ያህል ነው?

በዓለም አቀፍ መርህ የወሳኝ ኩነት አመዘጋገብ አሰራር በአንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ላይ ኩነት ሲከሰት በምዝገባ ህጉ በተሰጠው የመመዝገቢያ የጊዜ ገደብ ህጉ የማስመዝገብ ሀላፊነት የጣለበት ግለሰብ/ቦች ወደ ምዝገባ ጽ/ቤቱ በመሄድ ማስመዝገብ ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ገና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ልምድና ባህል ባልዳበረበትና የኩነቶች ህጋዊ መረጃዎች የሚሰጡት ጥቅም በህብረተሰቡ ዘልቆ ባልታወቀበት በየቤተሰቡ የሚከሰቱ ኩነቶችን በህጋዊው የጊዜ ገደብ በሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ይደረጋል የሚል እምነት አይኖርም፡፡ ከዚህም በላይ የምዝገባ ሥራውን አገልግሎት የሚሰጡ የምዝገባ ጽ/ቤቶች የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቃቸው በመሆኑ ሪፖርት የሚደረጉ ኩነቶችን በጽ/ቤት ተቀብሎ ከመመዝገብ ግልጋሎት ባሻገር ከኩነቱ መከሰት ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት የኩነቱን መከሰት ሪፖርት በማድረግ በምዝገባው ሥራ ሰፊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁም መሰረት የጤና ተቋማት፣ የአካባቢ ጤና ተጠሪዎች፣ የልምድ አዋላጆች፣ የልማትና የማህበራዊ አገልግሎት ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ዕድሮች፣ የጎሳ መሪዎች፣ . . . ወዘተ የኩነቶችን መከሰት ለቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ክፍል ሪፖርት በማድረግ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚጣልባቸው ናቸው፡፡

# V የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በማቋቋም የምዝገባ ተቋማት እና ዋነኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋና ዋና የተግባር ዘርፎች[7]

## 1. የሕግ አስፈፃሚ መ/ቤቶች፣ የትምህርትና የምርምር ተቋማት - ቁልፍ ሚና

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግን በመቅረጽ፣ እንዲተገበር በማድረግ፣ አተገባበሩን በመከታተል፣ በተለይ የህግ ዕውቀት ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ስለወሳኝ ኩነት ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች አጠቃቀም ለህግ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት ተገቢውን የአሠራር መመሪያ በማዘጋጀት፣ አፈፃፀሙን በመከታተል፣ በኩነቶች ምዝገባ ሥራ በመሳተፍ፣... ወዘተ በምዝገባው ተግባር ቁልፍ ሚና የሚኖራቸው ተቋማት ናቸው።

1.1 ፍትህ ሚኒስቴር፦ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባ ሕግ (Civil Registration Law) እንዲወጣና እንዲተገበር የማድረግ እንዲሁም አፈፃፀሙን የመከታተል ኃላፊነት እንዲኖረው መደረግ ይገባዋል። በተለይም የሀገራችን የምዝገባ ህግ አዘገጃጀትና አተገባበር በህገ-መንግስቱ ከተቀመጠው የፌደራልና የክልል መንግሥታት ህግ የማውጣት ስልጣንና ኃላፊነት አንፃር ምን ዓይነት አሠራር ሊከተል እንዲገባው የሚገልጽ እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያ ጭምር የማውጣት ኃላፊነት ይኖረዋል። የወሳኝ ኩነቶች

---

[7] *ማስታወሻ፦*

1. *በየተቋማቱ ሥር የተገለፁት የተግባር ዘርፎች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ቴክኒካዊ አሠራር ከሚጠይቀው የልዩ ልዩ ሙያዎች ጥምረትና የተቋማት የተቀናጀ የአሠራር አደረጃጀት አንፃር የተገለፁ ናቸው። በቀረበው ጽሁፍ የተገለፁት ተግባሮች ተቋማቱ ከሚከተሉት የአስተዳደር አደረጃጀት ጋር አልተገናዘቡም። በመሆኑም ወደፊት በሚዘጋጀው የምዝገባ የሥራ አመራርና አደረጃጀት መመሪያ ውስጥ የምዝገባ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን ቴክኒካዊ አደረጃጀት ከተቋማት ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም የፌደራልና የክልል አስተዳደር አደረጃጀት አንፃር በጥልቀት ታይቶ የሚቀርብ ይሆናል።*
2. *የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች የሰብዓዊ መብቶችን በማስከበር የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ መሆኑን በልዩ ልዩ የተባበሩት መንግስታት ቴክኒካዊ መመሪያ መጽሃፍቶች ተገልፆ ይገኛል። ይኸንን የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች የግልጋሎት ዘርፍ ስለሚያስፈፅሙት ተቋማት የተግባር ዘርፎች ወደፊት በሌላ ጽሁፍ ለማካተት ይሞከራል።*

ምዝገባ ሥራን በተሟላ መልኩ ለማካሄድ በምዝገባው ሥራ ላይ የሚሠማሩ መዝጋቢዎች፣ የምዝገባ ኃላፊዎች (ሹሞች) እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መሠረታዊ የህግ ዕውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ቀጣይና ቋሚ የህግ ዕውቀት ስልጠና የመስጠቱ ዋነኛ ኃላፊነት የሚጣለው በሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት ላይ ነው።

1.2 <u>የፍትህና ህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት፦</u> ኢንስቲትዩቱ ነባር ህጎችን በመመርመር እና ዓለም አቀፍ የምዝገባ ህግ አቀራረጽ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ የአቀራረጽ ሂደትን በማጥናት የምዝገባ ህግ ረቂቅን አዘጋጅቶ በማቅረብ ግንባር ቀደም ኃላፊነት እንደሚኖረው ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የምዝገባ ህግ ረቂቁን በማዘጋጀት ሂደት በተለይም የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ፣ የጤናና የአስተዳደር አካላት ሰፊ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን የህግ አቀራረጽ አሠራር በመከተል የምዝገባ ህጉን ረቂቅ ቀርጾ የማቅረብ ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ነው።

1.3 <u>ፍርድ ቤቶች፦</u> በፍርድ ቤቶች ውሣኔ ፍቺዎች ሲፈፀሙ ፍቺ መፈፀሙን የሚያረጋግጠውን የህግ ውሳኔ መረጃ ወደ ምዝገባ ጽ/ቤቶች በተከታታይ የሚተላለፍበትን ሥርዓት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል። ይኸም ፍርድ ቤቶች በምዝገባ ተግባሩ ውስጥ የሚኖራቸውን ሰፊ ተሳትፎ የሚያሳይ ነው። በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ከምዝገባ ሥርዓቱ የተገኙ የወሳኝ ኩነት ምስክር ወረቀቶችን በፍትህ አሰጣጥ ሂደቱ ማለትም በወንጀልም ሆነ በፍትሀ-ብሔር ጉዳዮች አግባባዊ የመረጃ ምንጭነታቸውን በመከተል ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግና የአጠቃቀም ሥርዓት በማደራጀት በኩል ሰፊ ድርሻ አላቸው።

1.4 <u>በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የሕግ የትምህርት ዘርፎች፦</u> በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች የተከፈቱ ቢሆንም በአንጋፋነቱ የሚጠቀሰው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። በዩኒቨርሲቲው ሥር የተዋቀረው የህግ ፋክሊቲ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የህግ አቀራረጽና

አወቃቀር ቀጣይ ተግባር ወሳኝ ድርሻ አለው። በተለይም የህግ ፋክሊቲው በህግ የትምህርት ዘርፍ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለውን የምዝገባ ህግ ከሀገሪቱ የሲቪል ህግና ተመሳሳይ ህጎች ጋር በተያያዘ ስለአቀራረጹ፣ አተገባበሩና በፍትህ አሰጣጡ የምዝገባ ሥርዓቱ ውጤት የሆኑ ህጋዊ የኩነት መረጃዎች አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨባጭ ትምህርቱን በመስጠት ተማሪዎች ከተግባር የመነጨ ዕውቀት እንዲጨብጡ በማድረግ ትልቅ ኃላፊነት የሚጣልበት ነው። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የህግ ትምህርት የሚሰጡ የግልና የመንግሥት ኮሌጆች የምዝገባ ህግ ምንነትን እና በሀገራችን ካለው የመንግስት አስተዳደር አንፃር ሊከተል የሚገባውን የአቀራረጽና የአተገባበር ዕውቀት ከተግባር ጋር በማቀናጀት ለተማሪዎችና ሰልጣኞች ትምህርት በመስጠት በቀጣይና ቋሚ የምዝገባ ተግባር የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚችሉ ምሁራንን የማፍራት ኃላፊነት የተጣለብቸው ተቋማት ናቸው።

## 2. <u>የስታትስቲክስና የጤና እንዲሁም የስነ-ህዝብ ጉዳይ አስፈፃሚ መ/ቤቶች፣ የትምህርትና የምርምር ተቋማት - ቁልፍ ሚና</u>

የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር መመሪያ፣ የአመዘጋገብ የቴክኒክ መመሪያዎችንና ልዩ ልዩ ቅጾችን በማዘጋጀት፣ በስልጠና፣ በምዝገባ ሥራው ግምገማ ጥናት በማድረግ ሰፊ ተሳትፎ ይኖራቸዋል። ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚጠናቀረውን የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃ አጠነቃቀር ድርጅታዊ አወቃቀር፣ የስታትስቲክስ መረጃውን ለመሰብሰብ አስፈላጊ የቴክኒክ መመሪያዎችና ቅጾችን በማዘጋጀት፣ የመረጃ ትንተናዎችን በማድረግ፣ መረጃውን በማሰራጨትና በመጠቀም ዋነኛ ባለቤቶች ናቸው።

2.1 <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት፡-</u> ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚያካሂደው የስታቲስቲክስ መ/ቤት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃን በተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የሚሰበስብ፣ የሚያጠናቅርና የሚያሰራጭ ማዕከላዊ ተቋም ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ረገድ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን በሀገሪቱ ለማቋቋም የሚያስችሉ

መሠረታዊ ጥናቶችን የማድረግና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን የማጠናቀር ኃላፊነት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራን እንዲያካሂድ በአዋጅ ለተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተሰጠ መሆኑ በማቋቋሚያ አዋጁ ላይ ተመልክቷል። የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አግባባዊ የመረጃ ምንጭ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ነው። ስታቲስቲክስ ግለሰባዊ ወይም ግላዊ መረጃዎች በጥቅል መረጃነት ለማጠናቀር የሚያስችሉ የመረጃ አሰባሰብ፣ የማጠናቀርና የማሰራጨት የዕውቀት/የሙያ ዘርፎች ባለቤት ከመሆኑ አንፃር በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች ምዝገባ የሚደራጁበትን ቴክኒካዊ ሥልትና የአመዘጋገብ መመሪያዎችን በጥናት ላይ ተመርኩዞ በማዘጋጀቱ በኩል ግንባር ቀደም ኃላፊነቱን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት እንዲወስድ መደረጉ አግባብ ነው።

በመሆኑም በምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ አወቃቀር ባለቤትና ተባባሪ የሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር በዋንኛነት የመዝገቦችን ቅርጽና ይዘት፣ የጽንሰ ሃሣቦችን ትርጉም፣ የመዝገቦችና ቅጾች አመዘጋገብ መመሪያን፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ እንዲሁም ተጓዳኝ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ከምዝገባው ህጋዊ አሠራር ጋር በማገናዘብ በማዘጋጀት ረገድ ጽ/ቤቱ ሰፊ ድርሻ ይኖረዋል። እንዲሁም በምዝገባው ሥራ የሚሳተፈውን የሰው ኃይል በማሠልጠን፣ የምዝገባውን ቴክኒካዊ አሠራር በመስክ በመቆጣጠርና ከምዝገባው የሚገኙትን መረጃዎች በመተንተን፣ በማጠናቀርና፣ ለተጠቃሚዎች በማሠራጨት፣ አልፎም በምዝገባው የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለልዩ ልዩ አስተዳደራዊና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስለመረጃዎቹ አጠቃቀም ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት ከኃላፊነቱና ተግባሮቹ አንዱ ይሆናሉ። የምዝገባውን ጥራትና የሽፋኑን ደረጃ በተመለከተም የተለያዩ ሳይንሳዊ የግምገማ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥናት በማድረግ ምዝገባውን በሀገር አቀፍና አነስተኛ የአስተዳደር ደረጃዎች በመገምገምና በውጤቱም መሠረት የምዝገባውን ድክመትና ጥንካሬ በመጠቆም የማሻሻያ ሃሣቦችን

በማቅረብ ረገድ ስፊ ኃላፊነት የሚጣለው በጽ/ቤቱ ላይ ነው። በሌላም በኩል የምዝገባው ህግ ረቂቅ ሲዘጋጅ ከሚመለከታቸው የህግ አካላት ጋር በመሆን በህጉ ዝግጅት በተለይ የሥርዓቱን የስታትስቲክስ መረጃዎች ከምዝገባ ሥርዓቱ የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና በሀገር አቀፍ ደረጃና በየአስተዳደር ዕርከኖች የማሠራጨት ሥራ ነው። ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ተገቢውን ጥቅም ለመስጠት የሚችለው በሽፋኑ እና በጥራቱ የተሙዋላ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር ሲኖር ነው። በዚህ ረገድ የምዝገባ ሥርዓቱ የሽፋንና የጥራት ደረጃ የተሙዋላ መሆኑን የተለያዩ የአጠናን ዘዴዎችን በመጠቀም መገመገም፣ የግምገማውንም ውጤት መሠረት በማድረግ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ሙያዊ የመወያያ መድረኮችን በመፍጠር ግኝቱን ማስተዋወቅ በተለይም የምዝገባው ሥራ በአጭር ጊዜ በጥራቱና በሽፋኑ የተሙዋላ ሊሆን ስለማይችል ህብረተሰቡና መንግስት ተገቢውን ጥረት እንዲያደርጉ ከመረጃው ጥቅም አንፃር ትምህርትና ቅስቀሳ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ከስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ ፍላጎት ባሻገር የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች ዋነኛ ተጠቃሚ የጤናው ዘርፍ ነው። በዚህ ረገድ በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንዲሁም በህብረተሰቡ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ፍላጎት ዋነኛው ምንጭ ለሕዝብ ጤና አገልግሎት ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር ነው። በመሆኑም ከምዝገባ ሥርዓቱ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር በኩል በየአስተዳደር ዕርከን ደረጃው ያሉ የጤና ተቋማት በምዝገባውና በስታትስቲክስ ጥንቅሩ ተግባር በቅርበት መሳተፍ ስለሚገባቸው የቆጠራው ጽ/ቤት የጤና ተቋማቱ በየተግባር ዕርከኖቹ እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት ይጠበቅበታል።

2.2 <u>ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን፡-</u> ቀደም ሲል ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ሊያከናውን የነበረው የሕዝብና ቤት ቆጠራና ተዛማጅ የጥናት ሥራዎች ራሱን ወደቻለ መ/ቤት ሊደራጁ ህገ-መንግስቱን መነሻ ያደረገ ምክንያት ነበራቸው። ይኸም ቢሆን ሁለቱ መ/ቤቶች በአደረጃጀት ይለዩ እንጂ በሙያና በአሠራር

ሁለቱም የስታትስቲክስ መ/ቤቶች ናቸው። በተለይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን በሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ሴክተር የስታትስቲክስ ጥናቶች መሠረታዊ የስነ-ህዝብ መረጃዎችን በማካተት መሰበሰቡ የግድ ነው። እነዚህን ግለሰባዊ የስነ-ህዝብ መረጃዎች ለምሳሌ ስም፣ የዝምድና ዓይነት፣ ፆታ፣ ዕድሜ እና የመሳሰሉ ግለሰባዊ የስነ-ህዝብ መረጃዎች በትክክልና በተሟላ አኳኋን ሊያገኝ የሚችለው የምዝገባ ሥርዓቱ ወቅታዊና ቀጣይ የኩነቶች መረጃዎችን ሲያደራጅ ነው። በመሆኑም የባለሥልጣን መ/ቤቱ ለምዝገባ ሥርዓቱ መቋቋምና በተለይም የኮሚሽኑን ጽ/ቤት በማገዝ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

2.3 <u>ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፦</u> ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከምዝገባ የሚገኘውን ግለሰባዊና ጥቅል የኩነቶች መረጃ ተጠቃሚ ከሆኑ ተቋማት አንዱና ዋነኛው እንደመሆኑ መጠን የጤናውን ዘርፍ የመረጃ አጠቃቀም አደረጃጀትና ዕውቀት ብቃትን የማሳደግ ኃላፊነት አለበት። ከዚህም በላይ በየሆስፒታሉና በየክሊኒኩ በየቀኑ የሚከሰቱ ልደቶችና ሞቶችን እያንዳንዱ የመንግስትም ሆነ የግል የጤና ተቋም የሜዲካል ምስክር ወረቀት በማዘጋጀትና ወዲያው ለባለጉዳዩ በመስጠት ረገድ በምዝገባ ህጉ በሚደነገገው መሠረት የማስፈፀም ኃላፊነት የሚጣለው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ነው። በጤና ተቋማት የተፈፀሙ ወሳኝ ኩነቶች መረጃ በአንዳንድ ቅጂ ለምዝገባ ጽህፈት ቤት እንዲደርሱ በማድረግ በምዝገባው አሠራር ላይም ሰፊ ድርሻ አለው። ይኸም ተግባር በተለይ በጤና ተቋማት የሚከሰቱ የልደትና የሞት ኩነቶችን የምዝገባ ሽፋን በማጠናከር ረገድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያበረክት ከሚችለው ትልቁ ኃላፊነት አንዱ ነው። እያንዳንዱ የመንግሥትና የግል የጤና ድርጅት በያለበት ይህንን ተግባር እንዲፈጽም በሕጉም ስለሚደነገግ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም አሠራሩን በማስተባበርና በመቆጣጠር፣ ለዚህም ተገቢ የአሠራር መመሪያዎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ የሥራ ድርሻ ይኖረዋል። ከዚህም በተጨማሪ በየሆስፒታሉና የጤና ድርጅቶች ወሳኝ ኩነቶቹ የተፈፀሙባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች በየምዝገባው ጽህፈት ቤት በመገኘት ኩነቱን እንዲያስመዘግቡ በማስተማርና በመቀስቀስ በተለይም ሕብረተሰቡ ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙ

የኩነቶች መረጃ ከህግ ግልጋሎት በተጨማሪ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን እንዲገነዘብና ዕውቀቱም እንዲጐለብት የማድረግ የሥራ ድርሻ ይኖረዋል። በሌላም በኩል ከምዝገባ ሥርዓቱ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የሚጠናቀሩ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ (Vital Statistics) መረጃዎችን ከሀገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ብቃትን በመገምገም በኩል መረጃውን በመጠቀሙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዋረድ አደረጃጀቱንም ጨምሮ የቀዳሚነቱን ሥፍራ ይይዛል። ከዚህም በላይ በተለይ የሞት ምክንያት መረጃን በመመዝገብ በኩል በጤና ተቋማት የተከሰቱ ሞቶችንና ከጤና ተቋማት ውጪ የተከሰቱ ሞቶችን በመለየት ትክክለኛ (ለህግ ሥርዓት አፈፃፀምና ለጤናው ዘርፍ የመረጃ ፍላጎት) መረጃ በመሰብሰብና በማጠናቀር ሰፊ የምዝገባ የኃላፊነት ድርሻ በሚ/ር መ/ቤቱ ላይ ሊወድቅ ይችላል። በአጠቃላይ በጤናው ዘርፍ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃዎች አጠነቃቀርና አጠቃቀም አሠራር ብቃት እንዲኖረው ለማድረግ ተገቢውን ዝግጅት የማድረግና የጤና ግልጋሎት አሰጣጥ የግለሰብና ጥቅል የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች ላይ እንዲመሠረት የማድረግ ኃላፊነት የተጣለው በሚኒስትሩ መ/ቤት ላይ ነው። በዚህ ረገድ ሚኒስትሩ መ/ቤት በየደረጃው ከሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤቶችና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ጋር ተቆራኝቶ መሥራት፣ በተለይም በምዝገባ የመረጃዎች አጠቃቀም አደረጃጀት መመሪያ ዝግጅትና የዕለት ተዕለት የምዝገባ ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል። የሚኒስቴሩ መ/ቤት የፌደራል ተቋም እንደመሆኑ መጠን ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያከናውነው የክልል እና የተዋረድ የጤና ተቋማትን አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ነው።

2.4 <u>የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽህፈት ቤት፦</u> የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግና ውጤቱንም ለመገምገም እንዲሁም አፈፃፀሙን ለመከታተል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት የሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በኢትዮጵያ ስነ-ሕዝብ ፖሊሲ ዶክሜንት ውስጥ

ከሠፈሩት ተግባሮች አንዱ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን የማቋቋም አስፈላጊነት ይገኛል። በመሆኑም የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሰው ኃይል፣ በገንዘብና በማቴሪያል የሚጠናከርበትን ሁኔታ በመፍጠር ረገድ ጽህፈት ቤቱ ከሌሎች ከሚመለከታቸው መንግስታዊ፣ አህጉራዊና አለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር በቅርበት መሥራት የሚገባው መሆኑ ግልጽ ነው።

2.5 <u>በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ ሥልጠናና ምርምር ተቋማትና የትምህርት ዘርፎች፡-</u> የሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ ምርምርና ስልጠና ተቋማትና የትምህርት ዘርፎች በሥነ-ሕዝብ ስታትስቲክስ የሙያ ዘርፍ ውስጥ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ (Vital Statistics) ትምህርትን ከተግባር ጋር በማያያዝ በማስተማርና በሀገሪቱ የምዝገባ ሥርዓቱን ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት በሚያግዝ መልኩ የተማሪዎችን ዕውቀት ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል። ተቋማቱ በተጨማሪ በምዝገባ ሥራው ላይ የተሠማራውን የሰው ኃይል በማሠልጠን፣ የምዝገባ አሠራር ምርምሮች በማካሄድ፣ የጽንሰ ሃሣቦች ትርጉሞችና መመሪያዎችን የሚያዳብሩ ከተግባር የመነጩ ዕውቀቶችን በማፍለቅ፣ ሙያዊ ስብሰባዎችና ወርክሾፖችን በማካሄድ፣ አልፎም ከአገሪቱ ባህልና ልማድ ጋር የተገናዘበ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ የአሠራር ሥርዓት የሚደራጅበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሽፋን የተሟላ እንዲሆን፣ ከዚህም በሽፋኑና በጥራቱ የተሙዋላ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦትና አጠቃቀም የአሠራር ሥርዓት በሀገሪቱ እንዲዘረጋ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በአሁኑ ወቀት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ በዋነኝነት ይኸን ኃላፊነት ሊወጣ የሚችለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥር የተቋቋመው የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ (ዲሞግራፊ) ስልጠናና ምርምር ማዕከል ነው።

2.6 <u>በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የህዝብ ጤና አጠባበቅ የስልጠናና ምርምር ተቋማትና የትምህርት ዘርፎች፦</u> ቀጣይና ቋሚ ግለሰባዊ የኩነት መረጃዎችና የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ (የልደት እና ሞት ምጣኔዎች) መረጃዎች ለጤናው ዘርፍ የጤና አገልግሎት ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም መሠረቶች ናቸው። ምንም እንኳ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃ የማጠናቀሩ ሥራ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ መ/ቤቶች ቢሆንም በምዝገባ ሥርዓቱ መረጃውን በመሰብሰብና በማጠናቀር ከስታቲስቲክስ ጽ/ቤቱ ጋር በቅርብ መሥራት የሚገባቸው የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የስልጠናና የምርምር ተቋማት ናቸው። በዚህ ረገድ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ሥልጠና የሚሰጡና ምርምር የሚያካሂዱ ተቋማት በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረተ የጤና ግልጋሎት ለመስጠት የሚችል ብቃት ያለው የጤና ባለሙያ የማፍራት ኃላፊነት አለባቸው። የጤና ትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ተቋማቱ አሰልጥነው የሚያወጧቸው የጤና ምሁራንም ሆኑ የሚያደርጓቸው የምርምር ተግባራት የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት ከማዕከል ጀምሮ ትንሹን የአስተዳደር ክፍል አልፎም ግለሰቦችን ለመለየት በሚያስችል ዘመናዊ የጤና አገልግሎትና አቅርቦት አደረጃጀት ሊመራ/ሊሠራ በሚችል ዕውቀት ላይ ትምህርቱ፣ ስልጠናውና ምርምሩ እንዲያተኩር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ በሀገራችን በጤናው ዘርፍ ስልጠና የሚሰጡ ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ሥር እንዳሉ የሚታወቅ ነው።

2.7 <u>የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት፦</u> በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በትክክል ከተካሄደ በየወሩ፣ በየሩብ ወይም ግማሽ ዓመት እና በየዓመቱ ቀጣይና ቋሚ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ በማስገኘት በኩል ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ውጭ አማራጭ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የሌለ መሆኑን ጽ/ቤቱ ያምናል። በመሆኑም የምዝገባ ሥርዓቱ በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች እንዲቋቋምና በሽፋኑና በመረጃ ጥራቱ የተሙዋላ እንዲሆን በማድረግ ከፍተኛ የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የሰው ኃይል ስልጠናና የምክር አገልግሎት ዕርዳታዎችን ድርጅቱ ሲያደርግ

የቆየና በማድረግ ላይ ያለ መሆኑን በሚያሣትማቸው መጽሔቶችና በሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች በየጊዜው እየተገለጸ ይገኛል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት በገንዘብ፣ በባለሙያና በሌሎች ማቴሪያሎች ከፍተኛ ዕገዛ እንደሚያደርግ ታውቆ ድርጅቱ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ በመንግስት በኩል መጠየቅ ያስፈልጋል።

3. <u>የአስተዳደር መ/ቤቶች፣ የሃይማኖትና ባህላዊ ማህበራት - ቁልፍ ሚና</u>

የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅርን በክልሎች በመዘርጋት፣ በበጀት፣ በማቴሪያልና በሰው ኃይል በማደራጀት፣ የምዝገባውን ተግባር (ወሳኝ ኩነቶችን በመመዝገብና ህጋዊ የምስክር ወረቀቶችን መስጠት እንዲሁም የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን መመዝገብ) በመፈፀም፣ የምዝገባውን ሽፋንና የመረጃውን የጥራት ደረጃ የተሟላ በማድረግ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በህግና አስተዳደር ግልጋሎት አሰጣጥ የወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊ የህግ መረጃዎችንና የስታትስቲክስ መረጃዎችን በክልሉ አደረጃጀት ላይ የተመሠረተ ወጥ የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓት መመሪያን በማዘጋጀትና ተግባራዊነቱን በማረጋገጥ፣ . . . ወዘተ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ተቋማት ናቸው።

3.1 <u>የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፦</u> የሚኒስትሩ መ/ቤት በክልል የምዝገባ ሥራውን የመምራትና የማስተባበር እንዲሁም አስፈላጊ ሀገር አቀፍ የአፈፃፀም መመሪያዎችን በማውጣት ሰፊ እገዛ እንደሚያደርግ ይጠበቃል። በክልሎች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራ በክልል መስተዳድር ጽ/ቤቶች ዕር እንደሚሆን በጠበቅም ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቴክኒካዊ አሠራር አንፃር አስተዳደራዊ አደረጃጀቱ በክልሎች ሊከተል የሚገባውን ከሚመለከታቸው ጋር ጥናት በማድረግ በምዝገባ ህግና በተገቢው ቴክኒካዊ መመሪያ እንዲከተት ያደርጋል። በዚህ ረገድ የክልል የምዝገባ አፈፃፀም አደረጃጀት ሀገር አቀፍ ይዘቱን እንዲጠብቅ ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑ ሚኒስቴር

መሥሪያ ቤቱ የምዝገባውን ሥራ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ በማስፈፀም በርካታ ተግባራት እንደሚጠበቁበት ለመረዳት ይቻላል።

ይኸንንም ተግባር ሚኒስትር መ/ቤቱ በተለይ ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፖሊሲ አማካሪ ኮሚቴን በመምራት ጭምር ሃላፊነት በመቀበል የምዝገባ ሥርዓቱን በማቋቋምም ሆነ በቀጣይነት የመረጃዎቹን ጥራትና የምዝገባ ሽፋኑን በማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለ።

3.2 <u>የክልል መንግሥታት መስተዳድር ጽ/ቤቶች፦</u> በማዕከል በሚዘጋጀው መርሀ ግብርና በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ አደረጃጀት መመሪያ ላይ በመመሥረት በየክልሉ የምዝገባ ተቋማትን መዋቅርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራርን የማደራጀትና የመምራት ኃላፊነት አለባቸው። ለዚህም ከክልል መስተዳደሩ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ክፍል የሚደርስ አስተዳደራዊ መዋቅር ይዘረጋል። የምዝገባው ሥርዓት አወቃቀር ያልተማከለ እንደመሆኑ መጠን በክልሎች የሚካሄደውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በምዝገባ መመሪያውና በምዝገባ ሕጉ መሠረት መካሄዱን መከታተልና መቆጣጠር የክልል መስተዳድር ጽ/ቤቶች ዋነኛ ተግባር ነው። ምዝገባው በቀበሌ መስተዳድሮች ሥር በሚዋቀሩ የምዝገባ ዋና ክፍሎች የሚከናወን በመሆኑ የክልሉ እና የተዋረድ አስተዳደሩ የምዝገባ አሠራሩን ዕለት በዕለት ተከታትሎ የሚከሰቱትን ችግሮች በመፍታት ምዝገባው በሽፋኑና በመረጃ ጥራቱ የተሟዋላ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም በላይ የምዝገባው ተግባር ቀጣይና ቋሚ በመሆኑ የምዝገባውን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አሠራር የተከተለ ቋሚ የምዝገባ አደረጃጀት በመስተዳድሩ የአስተዳደር አወቃቀር እንዲካተት የማድረግ ኃላፊነት የክልል መስተዳድር ጽ/ቤቶች ነው። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር ቀጣይና ቋሚ በመሆኑ የምዝገባውን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አሠራር የተከተለ ቋሚ የምዝገባ አደረጃጀት በመስተዳድሩ የአስተዳደር አወቃቀር እንዲካተት የማድረግ ኃላፊነት የክልል መስተዳድር ጽ/ቤቶች ነው። የወሳኝ ኩነቶች

ምዝገባ አሠራር ቀጣይና ቋሚ እንዲሁም በሽፋኑ የተሟላ ለመሆን በምዝገባ ህግ መደገፍ ይገባዋል። ለዚህም ነው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራ አስገዳጅ ህግ ሊወጣለትና ህጉም ሊተገበር የሚገባው። በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ አቀራረጽ በህገ-መንግስቱ የፌደራልና የክልል መንግስታት ህግ የማውጣት የስልጣን ክፍፍል መርሆ ላይ በመመሥረት የሚከናወን ነው። በመሆኑም የክልል መንግስት መስተዳድር ጽ/ቤቶች የህገ-መንግስቱን መርሆዎች በመከተል የምዝገባ ህጉን ከመተግበር ባሻገር የመቀረጽ ኃላፊነት ጭምር ሊጣልባቸው እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የክልል መስተዳድሮች የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

- የምዝገባ መዝገቦችና ሌሎች ዶክመንቶችን በማተም ወደየቀበሌዎቹ የምዝገባ ጽህፈት ቤቶች መላክ፣ መድረሳቸውንም መከታተልና መቆጣጠር፣
- ወሳኝ ኩነት የተመዘገበባቸው መዝገቦች ቅጂ ስለምዝገባው የመረጃዎች አቀማመጥ በተዘጋጀው የአሠራር መመሪያ መሠረት ወደሚመለከታቸው አካላት መላካቸውን መከታተል፣
- አዳዲስ የምዝገባ ጽህፈት ቤቶች ማቋቋም ሲያስፈልግ ይኸንኑ በማጥናት አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ መመሪያ የመስጠትና አተገባበሩን የመከታተል፣
- ምዝገባ በሚካሄድባቸው ቀበሌዎች የምዝገባ አሠራሩ በተዘጋጀው የአመዘጋገብ መመሪያና በምዝገባ ህጉ በመመራት እየተፈፀመ መሆኑን በየጊዜው መገምገምና ማሻሻያዎችን ማድረግ፣
- ስለምዝገባው አሠራር የወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የቴክኒክና የአስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በየደረጃው ማቋቋም፣
- ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙ ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች በህግ ጉዳዮች አፈፃፀም፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎት አሰጣጥ በግለሰቦችና በሕብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ህብረተሰቡን ያለማቋረጥ ማስተማር፣ መቀስቀስ፣

- የምዝገባ ሥርዓት ማስፈፀሚያ ሕግና ደንብ እንዲሁም ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ከመቅረጽ አንስቶ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣
- ለምዝገባው አስፈላጊውን በጀት በማጥናት መመደብ፣
- ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ አመሰራረትና እድገት የድርጊት መርሆዎችን በመከተል በክልሉ የምዝገባ ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሌሎች በምዝገባው ሥራ ተሳታፊ የሚሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር፣ ስለተሳትፎአቸው የሚገልጽ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የሥራ መመሪያ ማዘጋጀት፣

3.3 <u>የቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች፦</u> በየትኛውም ክልል የመጨረሻው የአስተዳደር ዕርከን የቀበሌ አስተዳደር ነው። በከተማና በገጠር የአስተዳደር አደረጃጀት የቀበሌ መስተዳድሮች ከቤተሰቦችና ከግለሰቦች ጋር ለመገናኘት ብቸኛና አመቺ የአካባቢ አስተዳደር አደረጃጀቶች ናቸው። በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት ይኸንኑ የገጠርና የከተማ ቀበሌ አስተዳደር መዋቅሮችን ተከትሎ የሚደራጅ ነው። በመሆኑም በከተሞችም ሆነ በገጠር ግለሰባዊ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባዎች የሚካሄዱት በቀበሌ አስተዳደሮች ሥር በሚዋቀሩ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባ ዋና ክፍል ነው። ምንም እንኳ በቀበሌዎች ሥር የሚዋቀሩት የምዝገባ ዋና ክፍሎች በቴክኒካዊ አሠራራቸው ራሳቸውን የቻሉ ቢሆኑም አስፈላጊ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊሟሉላቸው የሚችለው በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ነው። ስለሆነም በማዕከል በሚዘጋጀው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ድርጅታዊ አወቃቀርና ተግባርና ኃላፊነት መመሪያ መሠረት የገጠርና የከተማ ቀበሌ መስተዳድሮች የምዝገባውን ተግባር በመፈፀም ወሳኝ ድርሻ አላቸው።

3.4 <u>ብሄራዊ የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት፦</u> የማዕከል መ/ቤቱና ተዛማጅ ተግባር የሚያከናውኑ የክልል የሥራ ዘርፎች ከተሞችን

በጥላን በመገንባት በሚያደርጉት የዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም የቤቶችንና የነዋሪዎችን ማንነትና አድራሻ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ የሚገነዘቡት ጉዳይ ነው። ለዚህም ከኩነቶች ምዝገባው የሚገኙት የወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊ መረጃዎች ዋነኛ ግብዓት በመሆን ያገለግላሉ። በዚህ ረገድ የነዋሪዎች መታወቂያ አሰጣጥ፣ የቤቶች ቁጥር አሰጣጥ፣ የመንገዶች ስም አሰጣጥና መሰል ዘመናዊ የከተሞች አደረጃጀት በህጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎች ላይ እንዲመሠረት ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኘው መረጃ ወሳኝ ነው። ከዚህም በላይ በከተሞች የጤናና የትምህርት አገልግሎት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮች የመዘርጋት ሥራ፣ የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት፣ ...ወዘተ ዕቀድ ለማዘጋጀትና አፈፃፀሙን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለመከታተል መሠረቱ ቀጣይና ቋሚ ግለሰባዊ የህግ መረጃዎችና የሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ መረጃዎች ናቸው። በመሆኑም በከተሞች የሚቋቋመውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አደረጃጀትና የምዝገባ አፈፃፀም በመከታተል፣ በመቆጣጠር፣ በሃብና በማቴሪያል አስፈላጊውን እርዳታ በመስጠት ምዝገባው በከተሞች ሽፋኑ የተሟላ እንዲሆን በከተሞች ልማትና ዕድገት ተግባር ላይ የተሠማሩ ተቋማት አስተዋፅኦ ወሳኝ ነው።

3.5 <u>የሃይማኖት ድርጅቶች፡-</u> የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አሠራር የሚዘጋጁ ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች ለግለሰቦችና ለማህበረሰቡ የሚያስገኙትን ጥቅም መሠረት በማድረግ የተለያዩ የዕምነት ተቋማት የየሃይማኖቱ መዕመናን ስለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃዎች ጥቅም በማስተማርና በመቀስቀስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም በላይ አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት የልደት (ክርስትና)፣ የሞት (የቀብር ሥርዓት)ና የጋብቻ ምዝገባዎችን ሃይማኖታዊ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ያከናወናሉ። በሃይማኖት ሥርዓቱ መሠረት የተፈፀሙትን የኩነት ምዝገባዎች የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀትም እንደሚያዘጋጁ ይታወቃል፡፡ እነዚህ በተቋማቱ የሚከናወኑ የሃይማኖት ሥርዓትን የተከተሉ ምዝገባዎች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ልምድ በሌለበት አካባቢ የወሳኝ ኩነት መከሰትን በማመልከት ትልቅ ጠቀሜታ

አላቸው፡፡ ስለሆነም ለምዝገባው አሠራር በሚወጣው የኩነቶች አመዘጋገብ መመሪያ መሠረት የሃይማኖት ተቋማት በተለይ የኩነቶችን መከሰት ለምዝገባ ጽ/ቤት በመጠቆም ተግባር ላይ እንዲሠማሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪ የጋብቻ ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ የሃይማኖት ተቋማት ጋብቻዎችን በምዝገባ ጽ/ቤት በመመዝገብ ሂደት የሃይማኖት ተቋማቱ የሰጡት መረጃ ዋነኛ የኩነት መከሰት ማረጋገጫ ሆኖ ይወሰዳል፡፡ በሌላም በኩል የመቃብር ስፈራዎችን አጠቀቃም በተመለከተ ከምዝገባ ጽህፈት ቤት የሞት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላመጡ ምዕመናን ብቻ ክፍት እንደሚሆን በማስታወቅ የሞት ኩነት ምዝገባ ሽፋንን በማሳደግ በተዘዋዋሪ መንገድ ግፊት በማድረግ ሁሉም የሀይማኖት ተቋማት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3.6 <u>ዕድሮች</u>፡- በየከተማውና በየገጠሩ ተስፋፍተው ከሚገኙት ሕዝባዊ ማህበራት ዋናውና ከአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል አልፎም ቤተሰብና አባል ጋር ቀጥተኛና የማያቋርጥ ግኙኘነት ያለው በተለምዶ መረዳጃ ዕድር በመባል የሚታወቀው ባህላዊ ማህበር ነው፡፡ ዕድሮች የተለያየ ይዘትና መልክ አላቸው፡፡ ዕድሮች ለሀዘንም ሆነ ለደስታ ከቤተሰቦችና ግለሰቦች ጋር ግኙኘነት ስለሚኖራቸው ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ በአካባቢውና በቤተሰቦች ሲፈፀም ወዲያውኑ ለምዝገባ ጽ/ቤት ማሳወቅ የሚችሉበት አሠራር እንደሚዘጋጅ ይጠይቃል። ይኸም አሠራር በምዝገባ ህጉ በግልጽ እንዲደነገግ ይደረጋል። የቤተሰብ አባል በሞት፣ በልደት፣ በጋብቻና በፍቺ ሲጨምርና ሲቀንስ በዕድር መዝገቦች ክስተቱ እንደሚመዘገብ ይታወቃል (ሆኖም የተሟዋላ ካለመሆኑም በላይ ትክክለኛ ስለመሆኑ በቂ ማጣራት ማድረግ ይጠይቃል)፡፡ በመሆኑም ዕድሮች በየቀበሌው ለተቋቋሙ የምዝገባ ጽሕፈት ቤቶች ይህንኑ የመዘገቡትን መረጃ በሌላ ቅጽ ሞልቶ በመላክ የምዝገባውን ሽፋን ከፍ በማድረግ በኩል ሰፊ ድርሻ አላቸው። ከዚህም ባሻገር እያንዳንዱን የዕድር አባልና ቤተሰብ በየቤታቸው የሚከሰተውን ልደት፣ ሞት፣ ፍችና ጋብቻ ሪፖርት እንዲያደርጉ በመቀስቀስ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። በተጨማሪም ዕድሮች በየጊዜው በሚያደርጉአቸው ስብሰባዎች የምዝገባው

ጽ/ቤት አባላት እየተገኙ ትምህርታዊ ቅስቀሳ እንዲያደርጉ መድረክ በማዘጋጀት ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## 4. የማስታወቂያና የትምህርት ሚ/ር መ/ቤቶች - ቁልፍ ሚና

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃዎች በዋነኝነት የግለሰቦችን ህጋዊ አቋም (Civil status) የሚያረጋግጡ ህጋዊ ሰነዶች ናቸው። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የምዝገባ ሽፋን መሙዋላት ትልቁ መሠረት ይኸው የኩነቶች ህጋዊ መረጃዎች ለግለሰቦች የሚሰጡት ጥቅም በግለሰቦችና በመንግስት በትክክል መታወቁ ነው። የምዝገባው ስርዓት ግለሰባዊ የህግ መረጃዎችን የማስገኘቱና ተጠቃሎ በስታትስቲክስ መረጃነት በየዕርከኑ ላሉ የአስተዳደር አካላት የተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕቅዶችን በማዘጋጀት፣ ግልጋሎት በመስጠትና የአገልግሎት አሰጣጥን በመገምገም የሚውሉ መረጃዎችን ማመንጨቱ ለምዝገባው አስፈላጊነትና የሽፋኑ መሙዋላት ትልቅ ምንጭ ናቸው። በዚህ ረገድ የተለያዩ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በተለይም ከህግና አስተዳደራዊ ግልጋሎት አሰጣጥ አንፃር የመረጃዎቹን አስፈላጊነት በመንተራስ እንደ አደረጃጀታቸው ወቅታዊ፣ ቀጣይና ቋሚ ትምህርት መስጠትና በመቀስቀስ ሰፊ ድርሻ ይኖራቸዋል።

4.1 <u>ማስታወቂያ ሚኒስቴር፡-</u> የሚኒስትሩ መ/ቤት በተለያዩ የሕግና የአስተዳደር ቦታዎች የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ህጋዊ መረጃዎች የሚያስገኙትን ጥቅም መሠረት በማድረግ ሕብረተሰቡን በማስተማር እንዲሁም በተለይም አንዳንድ ባህላዊ እምነቶች በምዝገባው አሠራር ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ለማስወገድ የሚፈፋዱ ትምህርቶችን በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች በማስተላለፍ የምዝገባው ሽፋን የተሟላ እንዲሆን በማድረግ ግንባር ቀደም ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ በሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያን መሠረት በማድረግ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የፕሬስ ድርጅቶች ስለምዝገባው ጥቅም የሚያስተዋውቁ፣ የሚያስተምሩና የሚቀሰቅሱ መድረኮችን በመክፈት ሕብረተሰቡን ሊያስተምሩ የሚችሉበትን ሁኔታ

በማመቻቸት በኩል የሚኒስትሩ መ/ቤት የማስተባበሩን ተግባር በመፈፀም ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት ነው፡፡

4.2 <u>ትምህርት ሚኒስትር፡-</u> የሚኒስትሩ መ/ቤት በየትምህርት ቤቱ ስለምዝገባው የሚያስተምሩ ፕሮግራሞችን በመክፈትና በተለይም በስነ-ህዝብና ስነ ዜጋ የትምህርተ ዘርፎች በካሪኩለሙ በማካተት ቋሚ ትምህርት በመስጠት ሰፊ ተሳትፎ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም ትምህርት ቤት የሚገባ ልጅ የዕድሜውን ልክ የሚያመለክት ህጋዊ የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ እንዲመዘገብ በማድረግ በኩል ት/ቤቶች ተገቢውን እንዲያደርጉ መመሪያ በማስተላለፍና አተገባበሩን በመከታተል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰፊ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ ከዚህም አልፎ መምህራንና ተማሪዎች በቤተሰባቸውና በአካባቢያቸው ወሳኝ ኩነት ሲከሰት በመጠቆምና በማስመዝገብ ሰፊ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በላይ በቂ የህግና የአስተዳደር ትምህርተ የተሰጣቸው መምህራን በመዝጋቢነት በሚኖሩበት ቀበሌ ሊያገለግሉ የሚችሉበት የምዝገባ አሠራር አደረጃጀት ሊፈጠር ስለሚችል በዚህ በኩል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በምዝገባው ሥራ ላይም ሰፊ ድርሻ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

5\. <u>የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት</u> በባህልና በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች በሴቶች ላይ የሚደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል። ከእንቅስቃሴዎቹ አንዱ የቤተሰብ ሕግን አሻሽሎ መደንገግ ነው። የቤተሰብ ሕግን ተግባራዊ ለማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ሥርዓትን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። የምዝገባው ሥርዓት መቋቋምና የሚገኘው መረጃ ለቤተሰብ ሕግ ተፈጻሚነት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ስለሚታወቅ የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት ለምዝገባው መጠናከርና ግብ መምታት ከፍተኛ ሚና መጫወት እንደለበት ይጠበቃል። ይኸውም የወሳኝ ኩነቶች እንዲመዘገቡ በማድረግ፣ የምዝገባው ሕግና ደንብ ከቤተሰብ ሕግና ደንብ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ፣ የምዝገባው ሥርዓት ከተቋቋመ በኋላ የሕብረተሰቡ በተለይ የሴቶች ትብብር እንዲገኝ በማስተማር፣ በመቀስቀስና፣ በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይኖርበታል።

## የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባ ሥርዓት ምን ዓይነት የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃዎችን ያስገኛል?

- የየዓመቱን የልደት መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- የየዓመቱን የሞት መጠን/የህፃናትንና የአዋቂዎችን እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት/ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- ለሞት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች መረጃን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- የየዓመቱን የጋብቻ መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- የየዓመቱን የፍቺ መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- የጋብቻ ዕድሜ ስርጭት መረጃን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ በተፈጥሮ ክስተቶች (በልደትና ሞት) የሚጨምረውንና የሚቀንሰውን የህዝብ ቁጥር በየዓመቱ አልፎም ባነሰ ጊዜ እስከ ቀበሌ አስተዳደር ለማስላት የሚያስችል መረጃ ያስገኛል፤
- የየዓመቱን የህዝብ ብዛት መረጃ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን ያስገኛል፤
- ...

በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ ፦

- ለምን ያስፈልጋል? ከህገ-መንግስት፣ ከፍትሀ-ብሄር ህግ፣ ከስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት፣ ... ወዘተ ጋር ያለው ትስስር ምንድነው?

- በኢትዮጵያ የኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶች ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ምን ዓይነት ሲሆን ይገባል?

- በህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት ምን ዝግጅት ተደርጓል?

- ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙ ግለሰባዊ የህግና የስታትስቲክስ መረጃዎች ፍሰት አደረጃጀት ምን ዓይነት ሲሆን ይገባል?

- የኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ተግባርን የሚያከናውኑ የመንግስት ተቋማትና ዋነኛ ተባባሪ ድርጅቶች የተግባር ዘርፎች ምንድናቸው?